በቅዱስ አባታችን ጠቢቃነድ ጽሙናዊ ቅዱስ አለዓዜ አምላክነ አሜን

ሐዲስ ኪዳን

1ኛ ሳምንት

ወንጌል ዘዮሐንስ

ስለ ሥራተ ሕይወት፣ ትሩፋት፣ ረድኤት፣ ተጋድሎ በመለከት ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ፍቁረ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

- ዮሐንስ ማለት ፍስሐ ጠቢብት ማለት ነው።
- አባቱ ዘብዴዎስ እናቱ ማርያም ባውፍልያ ይባላሉ።
- ከነሣ አጥማቂነት ተጠርቷል ማቴ 4፥21
- ሃገረ ስብከቱ ጽርዕ ናት የጻፈበት ቦታ ኤፌሶን
- የጻፈበት ቋንቋ ዕርዕ ናት /ዮናን/
- የጻፈበት ዘመን ጊዜ ባረገ በ30 /በ63 ዓ/ም
- ኔርን ቲማር በነገሠ በሰባት /ከ54 — 68
- ከ4ቱ አፍላጋት በፈለገ ኢፍራጥስ ይመስላል
- ከ4ቱ ነ/ዘመን በወርኃ ሀጋይ ይመስላል
- ከ4ቱ አንስተ ያዕቆብ በራሄል ይመስላል
- ዮሐንስ ለመጀመሪያ ጊዜ ጌታን ከሰሚዳ አስተጥቃ የሳለ እሱ ነው።
- መከራ ሳይሰቀት ከመስቀሉ ስር የተገኘና በዚህም እመቤታችንን በአደራ የተቀበለ ሐዋርያ ነው።
- በዓለ እረፍቱ ጥር 4 ቀን ነው። የተሰወረበት ማለት ነው። አብ አለው እስመ አነ ወለድኩክሙ በትምህርተ መስቀሩ አለው በግብርም፣ በክብርም እሱ ይበልጣልና።
- ረድኤ አለው መጠኑ ለረድኤ ያለው የተፈጸመለት
- ተጋጋሪ በመለኮት፣ በድሕንነ መለኮት እየተቃኘ ምስጢረ ሥላሴን ይናገራልና፣ አንድም በግእዝ ቦታ የገባ ነው።

❖ ዮሐንስ ድንግል ሆይ ለምንልን፣ አማልደን፣ የመለኮትን ወንጌል ሰበክህ አባትህ ከቤተ መንግሥት ነው፣ እናትህም ከቤተ ክህነት ናት ስለዚህም አበ-ተለምሶስ ተባልህ ድጓ ገጽ 192

❖ የዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቅዳሴ መግቢያ ላይም ዮሐንስ ከቤተ መንግሥት፣ ከቤተ ክህነት ይወለዳል ብለው መተርጉማን ተናግረዋል።

❖ ዮሐንስ ማለት ፍስሐ ወንሴት ማቴ፡10፥3 ትርጓሜ መገነበ ቃላት ደግሞ የእግዚአብሔር ጸጋ ማለት ነው ይላል።

❖ ዮሐንስንና ወንድሙን ያዕቆብን ቦአኔርጌስ ማር፡3፥17 ብሏቸዋል። ደቂቀ ምሥጢር ማለት ነው።

Scanned with CamScanner

1 ፡ንላኔ ንንድነ፡ ተብሏል፣ ሰባቱ ንንድነ፡ የተጻንሩትን የምሥጢር ቃል ሰም፡ልና ፡ራ፡10፡4

2 ካ፡ቁረ እግዚእ /ጌታ፡ የሚወደው ደቀ መዝሙር/ ዮሐ፡13፡23፣ ዮሐ፡19፡26፣ ዮሐ፡20፡2፣ 21፡20

3. ታ፡ምለ-ጎስ /ቱምጎለ-ስ/ ይባላል ዮሐንስ ቱምለ-ጎስ እንዲል ድጓ ገጽ 192፣ በጾረኢ ቋንቋ ቱምለ-ጎስ ማለት በግዕዝ ነባቤ መለኮት ማለት ነው።

❖ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙም ምሥጢረ ሥላሴን ተንትኖ አብራርቶ ስለጻፈ ቱምለ-ጎስ/ ነባቤ መለኮት ተብሏል።

ሃያ፡አበ፡ ምዕ፡107፡18 ገጽ 484

❖ ኪ.ሜነ፡ልድ ክፍሌ በመገለገበ ቃላት ትክክለኛው ቱምለ-ጎስ ሲሆን ግድፈተ ጸሐፊ ነው።

4. አበ-ቀለምሲስ የጽርዕ ቃል ነው። በግዕዝ አበራእይ አበትንቢት ማለት ነው። ፈለዩ ነቢያት/ የተሰወሩ ነገሮችን የሚያይ ማለትም ይሆናል።

❖ ቅዱስ ያሬድ ዮሐንስ አበ-ቀለምሲስ ዘረፈቀ ውስተ ሕጽን ለኢየሱስ ብሎ-ቃል። ዳግመኛም ጥበብ ሐፀነተከ ከመጥብ፣ ልቡና ረስየተከ መከና፣ አእምሮ ታጌብረከ ሰምሀር፣ ወንጌለ መለኮት ሰበከ፣ ስምዐጽድቅ፣ ኮንከ፣ ወበእንተዝ አበ-ቀለምሲስ ተሰመይከ።-

ጥበብ እንደጡት አሳደገችህ፣ ማስተዋል ቦታዋ አደረገችህ፣ እውቀት ለማስተ-ማር አስገደደችህ፣ የመለኮትን ወንጌል ሰበክህ፣ የእውነት ምስክርን ሆንክ ስለዚህም አበ-ቀለምሲስ ተባለህ ብሎ ዘምሮለታል። ድጓ ገጽ፡192

❖ ቅዱስ ያሬድ ስለንጽህናው እና ስለድንግልናው ለትጉሐን ይኤምሮመ- እስመ ኀበረ ንጽሐ ምሳሌሆመ- ዮሐንስ ክቡር ሰባኪ ወንጌል መምህር ወድንግል።

ወንጌልን የሚሰብክ ክቡር፣ መምህር ድንግል ዮሐንስ መላእክትን ይመለከታቸዋል፣ በንጽሕና ከእነርሱ ጋር አንድ ሆኖአልና።

አጋዊከ ሐዋርያት ያሌዕሉከ በክብር፣ ማኅበረ መላእክት ይኤምኑከ በፍቅር፣ ወንጌላዊ ዮሐንስ ይዌድሱከ ሐዋርያት በእንተሥነ ግብርከ ወይትፈ ግዑ በጣዕመ ቃልከ ይዌድሱከ መላእክት እስመ ኀበርከ ንጽሐ ምስሌሆመ- ዮሀንስ ድንግል ሰባኬ ወንጌል ብሩህ ከመፀሐይ፣ ጽዳል ከመባሕርይ

ወንጌላዊ ዮሐንስ ሆይ ወንድሞችህ ሐዋርያት በክብር ከፍ ያደርጉሃል፣ ማኅበረ መላእክትም በፍቅር ሰላም ይሉሃል። ስለስነምግባርህ ሐዋርያት ያመሰግኑሃል። በቃልህም ጣዕም ደስ ይላቸዋል። መላእክቱም ያመሰግኑሃል በንጽሕና ከእነርሱ ጋር ተባብረሃልና ወንጌልንም የምትሰብክ ዮሐንስ ሆይ እንደ ፀሐይ ብሩህ ነህ እንደ እንቁም ታንጸባርቃለህ።

ጎረየከ አብ ወአማኅፀንከ ኅበወልዱ ጎረየከ ወልድ ወሰአመከ በእፉሁ አፍቀረከ አምአርዳኢሁ ወአርፈቀከ በእንግድአሁ ጎረየከ መ/ቅዱስ ወረሰየከ ሰረገላሁ ትሩፈኩሉ ምግባር ዮሐንስ መልኣከ ዘበምድር።

Scanned with CamScanner

አብ መርጦሃል ለልጁም አደራ ሰጥቶሃል።

ወልድም መረጦሃል በአፉም ስሞሃል፣ ከደቀመዛሙርቱም አብልጦ ወዶሃል፣ በደሬቱም ደስተምጦሃል፣ መ/ትዳቱም መርጦሃል፣ ማደሪያውም አድርጎሃል። መንፈሳዊውን ሥራ ሁሉ አብዝተህ የምትሠራ ዮሐንስ ሆይ ምድራዊ መልአክ ነህ ብሉታል።

ድጓ፡ ገጽ 191 - 192

፪/ የተማረበት ቦታ

- ሐዋርያት ጌታ ካረገ በኋላ ለማስተማር ዕጣ በሚጣጣሉበት ጊዜ ለቅዱስ ዮሐንስ ምድረ ጽርዕ /ግሪክ/ ደርሳዋለች። በዚያ ቦታ አርጤምስ ትመለክ ነበር። ዮሐንስ አልሄድም ብሉ ቅዱስ ጴጥሮስ አጽናንቶ ወስዶ አድርሶት ተመልሷል። ከዚያ በኋላ አርጤምስ የፈሰተ ዓርብ ፍጥረት መሆንዋንና አምላክ አለመሆኗን ሁሉን የፈጠረ አምላክ እግዚአብሔር መሆኑን አስተምሮ ጽርዓውያንን አሳምኗቸዋል።

ቅዱስ ያሬድ በኢፌሶን ስለማስተማሩ ሲናገር፡- ዮሐንስ ወንጌላዊ ከመቀርን ጼውአ ወአስተጋብአ አሕዛበ ብዙኃነ ቀርን ዘይጸርሕ ላቲ ለቤተክርስቲያን ቀርን ዘይኬልህ ወይጼውአሙ ለመሃይምናን ቀርን ዘይደምፅ ስብከተ በኤፌሶን

ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደመለከት ጮኽ ብሎ አሕዛብንም ሰበሰበ። ዮሐንስ ለቤተ ክርስቲያን የሚጮህላት መለከት ነው። የሚጮህና ምእመናንን የሚጠራ መለከት ነው። በኤፌሶን ስብከትን የሚያሰማ መለከት ነው ብሏል።

Scanned with CamScanner

2ኛ ሳምንት

ምዕራፍ አንድ

በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡- ሲል ዓለም ሳይፈጠር ዘመን ሳይቆጠር ሥነፍጥረት ከመጀመሩ በፊት ማለቱ ነው። ሊላው መጀመሪያ የሚለው ቃል ጊዜን አያመለክትም ከጊዜ ርቀት ነፃ ጊዜን ሊያመለክት አይችልም።

ማር፡ ዮሐንስ በመጀመሪያ ቃል ነበረ ማለቱ ከፍጥረታት ሲለይ ነው። እግዚአብሔር ያለመጀመሪያ ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ ካለው ለመለየት ነው ብሏል።

አነሳሱ ቃል በመጀመሪያ ነበረ የተባለው አካል ያለው በመሆኑ ነውና ዝርው ቃል ነበረ አይባልም።

ይህንም አስመልክቶ ጎርጎርዮስ ዘቂሳርያ ሃይ አበው ምዕ፡13፥22-24፡ ገጽ 42 ላይ ይህ ንነም ቃል አተርጋዋን፣ ቦርፎሪክን፣ አትሪክን ከተባሉት ከሦስቱ ቃላት ለይተን እናውተዋለን። እነዘህ ሰፍጥራን የተሰጡ ዝርዋን ቃላት ናቸው።

የአገዝ በግእዙ ትርንሚ ላይ መተርጉማን ዮሐንስ ወንጌሉን ሲጽፍ እንደሌሎች ደንጉላውያን በልደቱ አልጀመረም። ምክንያቱም የአማኞች ልቡና ፍጡር መስሏቸው በእሥላክነቱ ማመንን እንዳይተው ቀዳማዊነቱን በመጻፍ አምላክነቱን መናገር ወደደ ብለዋል።

ማር ዮሐንስም፡- ቃል ነበረ ብቻ ሳይል በመጀመሪያ ቃል ነበረ ማለቱ በመለኮት፣ ቡባሕርይ፣ በአኗኗር ከአብ ጋር አንድ መሆኑንና ቀዳማዊነቱን ያሳውቅ ዘንድ ነው ብሏል።

ስለምን ቃል ተባለ? ቢሉ ቃል የሚለው ስም ወልድን መግለጽ ስለሚችል ነው።

ሰዎች በልቡናቸው የሚያስቡትን ረቂቅ ምሥጢር በተለም በተጻፈ ጊዜ ግዙፍ ሆኖ ይታያል፣ ወልድም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በህልውና አንድ የሚሆን ረቂቅ ሲሆን በሥጋ ገንዘር ታይታልና።

- ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡- ማለት ቃል የተባለ ወልድ በእግዚአብሔርነቱ ከአብ ሳይለይ ይኖራል ማለት ነው።
- ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡- በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ካለ በኋላ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ገልጦ ተናገረ።
- ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡- ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ብለ- ከእግዚአብሔር አብ ጋር ያለውን አንድነት እንደገለጠ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ በማት ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን አንድነቱን ገለጠ።
- ሁሉ በእርሱ ሆነ፡- ፍጥረታት ሁሉ በእርሱ ቃልነት፣ በእርሱ ፈጣሪነት፣ በእርሱ ሕልውና ተፈጠሩ ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ሲያስረዳ "ነገር ሁሉ በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን"። 1ኛ ቆሮ 8፥6
- በእርሱ ሕይወት ነበረች /4/ ሰው ሁሉ በወልደ እግዚአብሔር ሕይወትን ማግኘታቸውን መናገር ነው።

Scanned with CamScanner

- መንገድና ሕይወት እኔ ነኝ /ዮሐ፡14፥6/ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ /ዮሐ፡11፥25/ ብሉ-ነበር፡፡
- ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች /4/ ብርሃን ማለት የሰው ሁሉ እውቀት ማስተሞር፡፡
- እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፡፡ ዮሐ፡12፥46
- ማር ዮሐንስ ይህን ለለሰው ልጅች በተፈጥሮ ስለሰጣቸው ጸጋ ተናገረ ይላል፡፡
- ብርሃንም በጨለማ ይበራል /5/ ብርሃንም የተባለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ መዝ፡42፥3፣ መዝ፡35፥9፣ መዝ፡96፥11፣ ኢሳ፡9፥1፣ ዮሐ፡8፥5፣ ዮሐ፡12፥36
- ጊዜማራ ገጽ 68 ብርሃን ውእቱ ዘያቀርቦመ ለእረፉን በምጽአቱ- ለው በመሆኑ የራሱትን የሚያቀርባቸው ብርሃን ነው ይላል፡፡
- ጨለማም አላሸነፈውም፡- ጨለማ የተባለ ዲያብሎስ ነው፡፡ በ3ቱ ፈተናዎች ቢፈትነውም አላሸነፈውም ማቴ፡4
- ሊላው ጨለማ ኃጢአት፣ ሞት፣ ስህተትን የተሞላው ዓለም ነው፡፡
- ለሰው ሁሉ የሚየበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም የመጣ /9/ የጌታ ብርሃንነት በትምህርቱ፣ በትሕትናው፣ በተዓምሩ በሥነምግባሩ ነው፡፡
- ዓለመም አላወቀውም /10/ ዓለም የተባለ የሰው ልጅ ነው፡፡ ክርስቶስ ባለማመናቸው
- ወደወገናቸው መጣ/፡1/ ወገኖቹ የተባሉ፡-

  1ኛ. የሰው ልጅ በሙሉ
  2ኛ. እስራኤል ናቸው } ሁሉም አላመነበትም

- የተቀበሉትን የእግዚአብሔር ልጆች ይባሉ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው /12/ ሥልጣን የተባለ ልጅነት ነው፡፡
- ገላ፡3፥26፡- በእምነት በክል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፡፡
- እነሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከሥጋ ፈቃድ አልተወለዱም /13/ አይሻዱ የተባለ ሊቅ ሰው በ3 ነገር ከእግዚአብሔር ይወለዳል፡፡

  1. በጥምቀት
  2. እግዚአብሔር ምሥጢራትን ሲገልጥለት
  3. በትንሣኤ ከክርስቶስ ጋር በመተባበር

Scanned with CamScanner

3ኛ ሳምንት

- ዮልያም ሥጋ ሆነ /14/ በመጀመሪያ ቃል ነበረ ብሎ ዓለሃ ሳያፈለጠር ሙኖሩን ተናፎ ያ ቃል ሥጋ የለበሰው ሰው የሆነው ነው ይላል።
- አትናቴሥስ፡- መከገመ ይተረጎም ነገሩ ለቅዱስ ዮሐንስ ዘይቤ ሙእላ ቃል ሥጋ ኮነ በነሚአሁ ለቃል ሥጋ እምእግዘአትነ ትድስት ድንግል ማርያም /ቃል ሥጋ ሆነ ዮሚለው የቅዱስ ዮሐንስ አነጋገር ከአመቤታችን ሥጋን ተዋህዶ ብሎ ይተረጎማል /ሃያ፡አበ፡ምዕ፡31፥5
- ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኖ አደረ /14/ ጸጋን ተመልቶ ማለት ከአመቤቻችን የነሣው ሥጋ የሚያድን ዓለምን የሚገዛ ሆነ ማለት ነው።
- ክኒኔ በኃላ የሚመጣው /15/ ጌታ መሰበክ የጀመረው ዮሐንስ አስተምሮ ከታሰረ በኃላ ነውና።
- ሉላው ዮሐንስ ጌታን በ6 ወር ይበልጠዋልና ማር ኤፍራም
- በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና /16/ በኦሪት ላይ ወንጌል በመንፈስ ረድኤት ላይ መንፈስ ልደት፣ በአእምሮ ጠባያዊ ላይ አእምሮ መንፈሳዊያን ገንዘብ አደረግን
- እግዚአብሔርን ያየው አንድስ እንኳን የለም /18/ እግዚአብሔር ከመታየት በላይ ነው።
- አንድ ልጁ እርሱ ተረከው /18/ የእግዚአብሔር አብን ህልውና የነገረን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
- እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ /ቁ 29/ እነሆ ማለት እመነበት. ተከተሉት
- ጌታ በበግ ይመሰላል ኢሳ፡53፥7፣ ኤር፡11፥19 ራእ፡14፥1
- ሁለቱ ቀደመላመርት ጌታን ተከተሉት /ቁ 37/ እንድርያስና ዮሐንስ ናቸው።
- የዮሴፍን ልጅ አገኘነው /45/ ማለት በቤተ ዮሴፍ ስላደገ፡- አይሁድ ወ/ዮሴፍ የሚሉትን ሙሴ በኦሪት የጻፈለት ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት ሆኖ አገኘነው።
- ከበለስ በታች አየሁህ /49/፡- ናትናኤል ከበለስ ሥር ተቀምጦ ሰባዔ ይቆጥር ነበርና፡-
- መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ /52/
  1. ሰውና መላእክት መታረቃቸውን
  2. ሰው አምላክ ሆነ አምላክ ሰው ሆነ እያሉ መነመራቸውን
  3. የመላእክት ፈጣሪ መሆኑን

Scanned with CamScanner

4ኛ ሳምንት

ምዕራፍ ሁለት

- በሦስተኛው ቀን ሠርግ ተደረገ፡- በ3ኛው ክፍለ ዘመን ሰው መሆኑ ጌታ አርባው ቀን ትዳሜ ይጨርሳል፡፡ እሁድ ወደ ዮሐንስ መጥምቅ ሄደ ዮሐ፡1፥29 ሰኞ ዮሐንስ ከ፪ ሰዓ ደቀመዛሙርት ጋር ቆሞ ላለ ጌታን አየው ዮሐ፡1፥35፡፡ ማክሰኞ ጌታ ፊሊጶስን አገኘው ፊሊጶስም ናትናኤልን ወደጌታ አመጣው ዮሐ፡1፥4 በዚህ ዕለት በገሊላ ሠርግ ተደረገ፡፡
- የኢየሱስ እናት በዚያ ነበረች፡- በትልቅ ሰው ልማድ ተጠርታ፣ ቤተዘመድ ናትና፡፡
- ጌታም፣ ደቀመዛሙርቱም ወደ ሀገር ታደሙ /1/ እናትን ጠርቶ ልጅን፣ መምህርን ጠርቶ ደቀመዛሙርትን መተው ሥርዓት አይደለምና፡፡

መጽሐፈ ግብረ ሕማማት ፡- የመ.ሽራው ስም ዶክማስ ወልደዮክን ይባላ፡፡ ጌታን የጠራው ናትናኤል ነው፡፡ ሠርጉን ይባርክለት ዘንድ፡፡ እመቤታችን እና ዮሴፍን ይጠሯቸው ዘንደ ሰዎችን ላክ ይላል፡፡

ሣር ዮሐንስ ግን አምላክነቱን ስላልተረዱ እንደማንኛውም ሰው ወደ ሠርግ ቤት ጠርተው ታል ብሏል፡፡

የኢየሱስ እናት የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው /3/ እመቤታችን ለወዳፈት ስለምትፈጽመው ምልጃ መጀመሪያ ነው፡፡ ምግባር፣ ሃይማኖት የላቸውም፡፡

- አንች ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ /4/ አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ማት ውኃውን ጠጅ አድርግላቸው ብትይኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ከአንቺ ጋር ምን ፀብ ወይም ተቃውሞ አለኝ፡፡ ይህን የመሰለ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "የይሁዳ ንጉሥ ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ" 2ኛ ነገ፡23፥29
- የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ 1ኛ ነገ፡17፥18
- ጊዜዬ ገና አልደረሰው /4/ ውኃውን ወደ ወይን የምለውጥበት፣ ተአምራት አድርጌ አምላክነቱን የምገልጥበት መቼ ተሰቅዬ ዓለምን የማድንበት
- ከሰማይ በታች ለሁሉም ጊዜ /ዘመን/ አለው መክ፡3፥1
- የግእዝ በእግዝ ትርጓሜ የወይን ጠጁ ፈጽሞ አላለቀም ነበርና ይህን አላት ይላል፡፡
- የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው /5/ ማሳሰቢያዋን እንደተቀበላት አውቃ
- ማር ዮሐንስ፡- እናቱ አገልጋዮቹን ማዘዟ ጊዜዬ ገና አልደረሰው ማለቱ ስለትሕትና እንጂ የሚሳነው ነገር እንደሌለ አውቃለችና ይላል፡፡
- የማንጻት ልማድ /6/ አይሁድ ርኩስ የሚሉትን ነገር ሁሉ እያጠመቁ ያነጹ ነበር፡፡ ዘጸ፡19፥11፥12 ጋኖቹ የረከሰ ሰው የሚታጠብበትን ውኃ የሚይዙ ናቸው፡፡

Scanned with CamScanner

- የወሰኑ ምሥክርነት፡- አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በመጽ/ ምሥክርነ "ይእዛ አስተብዕሎ በእንተ መደን ምድራዊ ውእቱኒ አዘራእኢ በእመሥዋዕትየበእንተ መደነ ደመ በደኅ-ኮኃሰ እምኃበኡ"
- እርሷ ስለምድራዊ መደን ለመነችው አሰ ከነኑ ስለሚፈሰው ደመ በምሥክርነ ነግራት ይላል።
- ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም እንደወጣና ከቤተ መቅደስ ገብቶ ገበያውን እንደፈታ የቀፈውን አንብቡ።

Scanned with CamScanner

5ኛ ሳምንት

ምዕራፍ ሦስት

- ኒቆዲሞስ፡- የጌታ ደቀመዝሙር፣ ጌታን የገነዘ
- ዘኦሪታውያን ወገን፡- በፋራስ ፊሪሳውያን ተብለዋል ማቴ፡23፥2
- የአይሁድ አለቃ፡- በዕውቀት፣ በሀብት፣ በስልጣን
- በሌሊት ወደ ጌታ መጣ /2/፡- በቀን ከሚመጡ ቀድሞ፣ የጨለማ ልብ፣ ከንቱ ወሬዳሴ ሽታ፣ ፈሪ
- እግዚአብሔር ከሱ ጋር ከሆነ በቀር /2/ ግእዝ በግእዝ የተረጎመ ሊቅ ኒቆዲሞስ ጌታን ያመሰገነው ታላቅ ሰውን ማመስገን በአይሁድ የተለመደ
- አለማመኑን፡- ከግላ አሪት አልተላቀቀም፡፡
- ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር /3/፡- ጌታ ለኒቆዲሞስ ምሁረ አሪት ስለሆነ፡- የማያውቀውን ምሥጢረ ጥምቀትንና ምሥጢረ ሥላሴን
- ከውኃና ከመንፈስ ስለመወለድ /5/፡- ሁለተኛ ስለመወለድ ነግሮት የሚወለድበትን አልነገውም ነበርና፡፡

የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ፡- ጥምቀት በውኃ መሆኑ ግን የሞትና የትንሣኤን ምሥጢር ለመግለጽ ነው፡፡ ማለት ወደ ውኃ ውስጥ መግባት ወደ መቃብር የመውረድ፣ ከውኃ መውጣት ከመቃብር የመውጣት የትንሣኤ ምሳሌ ነው ብለው ተርጎመዋል፡፡

ጌታ ከመንፈስ ቅዱስ እንድንወለድ ያዘዘን እሱ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ተወልዶ ነው፡፡

ማቴ፡1፥20፣ ሉቃ፡1፥35

የውኃና የመንፈስ ጎብረት የተከሰተው ዓለም በተፈጠረበት ዕለት በመጀመሪያው ቀን ነው፡፡ "የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍሮ ነበር"፡፡

ዘፍ፡1፥2 በውኃ ላይ መስፈፉ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በውኃ /በጥምቀት/ ለዘመነ ሐዲስ ሰዎች የሚሰጥ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ፡- ወሀሎ መ/ቅ ይጼልል መልዕልተማይ እምቅድመ ገዘንቱ ግብር ዘተፈጸመ በእንተ አነ ሃይ አበው፡ ምዕ፡87፥16

ሕዝቅ፡ 36፥25፡- ጥሩ ውኃን እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ አዲስ ልብ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ ብሎ ጥምቀት በውኃና በመንፈስ ቅዱስ መሆኑ አስረድቶ ነው፡፡

Scanned with CamScanner

- ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው /ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው /6/ ማለት ከ ሥጋ የተወለደ ሥጋን እንደሚመስል ሁሉ ከመንፈስም የተወለደ ወላጁ መንፈስ ቅዱስን ይመስላል ማለት ነው።
- ነፋስ ወደሚወድደው ይነፍሳል /8/ ለኒቆዲሞስ ከመቅ መወለድን ለማስረዳት ■ነፋስ መስሉ ያስረዳዋል።
- ነፋስ ድምጽ አለው መልኩ ግን አይታይም መንፈስ ቅዱስም ምሥጢር ይገልጣል፣ ቋንቋ ያናግራል። በበዓለ ሃምሳ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ሲወርድ በአውሉ- ነፋስ እምኻል ድምፅ ተሰምቷል። ሐዋ፡2፥2
- ነፋስ ምርቱን ከገለባው ይለያል፣
- ነፋስ ወደዚህ ዓለም የሚመጣው እየተለካ እየተመጠነ ነው። ዜናከ፡11፥8
- መንፈስ ቅዱስ፣ የሚሰጥ እየተለካ እየተመጠነ ነውና 1ኛ ቆሮ፡12፥4 - 11
ወበከመ ይደልዎ ይበቁየ እን
- ነፋስ ለሕይወት ለበረከት ይነፍሳል ዘፍከ 25፥4 መንፈስ ቅዱስም ሕይወትን በረከትን ይሰጣል ሚልከ 2፥15፣ ዮሐ፡ 6፥63
- ኤልያስ በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ወጥቷል 2ኛ ነገ 2፥11 መንፈስ ቅዱስም ቅዱሳንን ያወጣቸዋል፣ ይነጥቃቸዋል ግብ.ሐዋ፡8፥39
- አንተ የእስራኤል መምር ስትሆን ይህን አታውቅምን /10/
- ✧ የእስራኤል መምህር ስለሆነ ስለጥምቀት የተነገረውን ትንቢት ሕዝ፡36፥25፣ ዘካ፡13፥1፣ ሚክ፡7፥19 ላይ ያለውን ማወቅ
- ✧ ፈሪሳዊ በመሆኑ ምሁር ነኝ፣ አዋቂ ነኝ የሚል ስሜት ስለነበረ ማወቅ ያለብህን ገና አላወቅህም ሲለው ነው።
- የምናውቀውን እንናገራለን፣ ያየነውን እንመሰክራለን /11/፡- ስለሱ የመሰከሩትን ምስክሮች ወክሎ፣ ራሱን ከአብ፣ ራሱን ከዮሐንስ ጋር
- ስለምድራዊ ነገር ስነግራችሁ ካላመናችሁ ስለሰማያዊ ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ /12/
- በምድር የሚፈጸም ምሥጢረ ጥምቀትን ስነግራችሁ ስለትንሣኤ እንዴት
- ምድራዊ ልደቱን ስነግራችሁ ካላመናችሁ ሰማያዊ ልደቱን እንዴት
- ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም /13/
- ሰው መሆኑን፣ ሥጋ መልበሱን፣ በሥጋ መወለዱን
- ወደ ሰማይ በሥጋ እንደሚያርግ ሲነግራቸው ነው።
- መሌም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ /14/ ዘኁ፡21፥5-9
በብሉይ ኪዳን የተፈጸመው ሁሉ ለሐዲስ ኪዳን ምሳሌ ነው።
አርቄ ምድ
- እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ስለመስጠት /16/
- ዓለም በልጁ እንዲድን እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አላከውም /17/ የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ያላመኑት ግን ለራሳቸው የኩነኔ ምክንያት ይሆናሉ ይላል።

Scanned with CamScanner

- በእርሱ የሚያምን አያፈረድበትም /18/ አምኖ ሥራ ከሠራ
- በማያምን ግን አሁን ተፈርዶበታል /18/ ማር ዮሐንስ ንጠኢት የሚሰራ ሰው በዘለዓለም ከነኔ የለም ብሎ እንዳይጠራጠር
- መሻሩያቱ ያለችው እርሱ መሻሩ ነው /29/ እርሱ እንደመሻሩ ከእልፍኝ ይጠፋል። መዝ፡18፥5
- ሚዜው በመሻሩው ድምፅ እጅግ ደስ ይለዋል /29/ ዮሐንስ መጥምቅ
- እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል /34/ በእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ሰፊኑ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ መንጌልን ያስተምራል። እግዚእብሔር ወደዚ የሚላክ ሰው ነው የሚናገረውም ቃል ይኖረዋል
- ሁሉን በእጁ ሰጥቶታል /35/ በምጽአት ታይቶ ተገልጦ ይፈርዳል
- በልጁ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው /36/ የዘለዓለም ሕይወት መሠረቱ ማመን ነው።
- ማር ዮሐንስ፡- ሃይማኖትስ ሥራ ሊተባበራት ትፈልጋለች ሰው በሃይማኖቱና በሥራው መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳልና ብሏል።
- በማያምን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል /36/ አዳምና ሄዋን ዕፀ በለስን በበሉ ጊዜ የተቆጣው ቁጣ ዘፍ፡ 3፥10 ፈርዶ የሚያመጣው ፍርድ
- ማር ኤፍራም፡- የእግዚአብሔር ቁጣ የተባለ በዓለም ፍጻሜ ለኃጢአተኞች የሚያዘጋጀው ስቃኔ

Scanned with CamScanner

3. የሕያውነት ውኃን ልጅነት ኢሳ፡55፥1 ሕዝ፡36፥25 ራእ፡21፥6
4. ከአባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን /12/ አባታችን ማለቱ
   1. ከምርኮ የተረፋትን ከአሕዛብ ጋር ተጋብተዋል
   2. ምናሴ የተባለው ካህን ከአስተማረ በኋላ ያዕቆብ አቡነ ብለዋልና ለያዕቆን ያሏትን አከብሮት

- እኒ ከምሰጠው ውኃ የሚጠማ ሁሉ ለዘለዓለም አይጠማም /14/
  - ❖ አንድ ጊዜ የተሰጠን የልጅነት ጸጋ ለዘለዓለሙ የእግዚአብሔር ልጅች ሆነን
  - ❖ በሱ አማካኝነት ለሌላው ሲሰጥ ይኖራል
- ይህን ውኃ ስጠኝ ብትለው ባልሸን ጥሪ ብሏታል /15/ የተሰወረውን የሚያውቅ የባሕርይ አምላክ መሆኑን
  ባል የለኝም ማለቷ ጌታ ፍጡር መስሏት ስለነበረ
- እኛ ለምናውቀው እንሰግዳለን /22/፡-
  በስም፣ በግብር፣ በአካል 3 በባሕርይ አንድ ብለን
- ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል /23/ ጊዜ የተባለው ዘመነ ሐዲስ ነው፡፡ በእውነት ማለት አምላክነቱን ተረድተው ይሰግዳሉ፡፡
  ማር ዮሐንስ፡- በእውነት የሚሰግዱ የተባለ ከአይሁድና ከሳምራውያን ያመኑ
- በመንፈስ፡- ከመንፈስ ቅዱስ ተወልደው፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተሞልተው ይሰግዳሉ-፡፡
  ሌላው በሕሊና በሀሳብ ማት በጾም፣ በጸሎት / በሰቂለ ሕሊና
- ኢሳ፡26፥9፡- መንፈሰ በውስጠ ወደ አንተ ትገሰግሳለች
- ሉቃ፡1፥47፡- መንፈሰ በአምላኪ በመድኃኒቱ ሐሤት ታደርጋለች
- ሮሜ፡1፥9-10፡- በመንፈሰ የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነው፡፡
- እግዚአብሔር መንፈስ ነው /24/ ረቂቅ መሆኑን በኢየሩሳሌምና በሰማርያ ብቻ ያልተወሰነ መሆኑን /24/ ጌታ ይህን ያላት ሳምራዊቷን ከሥጋ ፈቃድ ሊያርቃት ነው፡፡ /ማር ዮሐንስ/
- ከ4 ወር በኋላ መከር ይመጣል /35/ በ4ኛው ክፍለ ዘመን ሥጋዌ መደረጉን
  ዘመነ አበው ከአዳም እስከ ሙሴ
  ዘመነ መሳፍንት ከሙሴ እስከ ዳዊት
  ዘመነ ነገሥት ከዳዊት እስከ እስራኤል ተማርከው ባቢሎን እስከወረዱበት
  ዘመነ ካህናት እስራኤል ከተማረኩበት ጀምሮ ክርስቶስ እስከተወለደበት
- የሚዘራና የሚያጭድ /36/ ነቢያት ሐዋርያት
- ሌሎች ደከሙ እናንተ በድካማቸው ገባችሁ /38/ ደከሙ የተባሉ ነቢያት በድካማቸው ገቡ የተባሉ ሐዋርያት

Scanned with CamScanner

7ኛ ሳምንት

ምዕራፍ አምስት

በዓለ ቅ[illegible]ንጠኮስጤ /በዓለ ሃምሳ

- የአይሁድ በዓል፡- አይሁድ በዓላቸውን የሚያከብሩት ታላላቁ ቤተመቅደስ ባለበት በኢየሩሳሌም ነው። የብሉይ ኪዳን በዓል እንደሚያልፍ፡ እያወቀ በዓላቸውን ያፈነከር ነበረ።
- አምስት መመላለሻ /2/ ወደ መጠመቂያው የሚያደርሱ 5 መንገዶች
  የአምስቱ አለማደ ምስጢር
  5ቱ በሽተኞች የ5ቱ ጾታ ምእመናን
- ተድላ የገባ አንድ አንድ ሰው በየሳምንቱ /4/ ፡- አንድ አንድ ሰው መዳኑ እስራኤል ተስፋ እንዳይቆርጡ
- 38 ዓመት የታመመ /5/ የመጻፅ ታሪክ ... አንድ ባይ መሆኑ በኦሪት ፍጹም ድህነት እንደሌለ
- ልትድን ትወዳለህን /6/ መዳን እንደሚወድ ጌታ ያውቃል
  የግእዝ በግእዝ ተርጓሚዎች መጻፅ ሃይማኖቱን ይገልጥ ዘንድ ነው
- ሰው የለኝም /7/ ብዙ ዘመን ከመታመሙ የተነሣ ሰው አርቶታል ማለት
- ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ /8/ አይሻዳድ ጌታ እንዲህ ማለቱ ተአምራቱን ያስረዳ ዘንድ ነው። ሰዎች ምትሐት ነው እንዳይሉ ለመታን ትንሣኤ ምሳሌ ነው ብሏል።
- ከዚህ የሚብስ እንዳያገኝህ ዳግመኛ ኃጢአት አትሥራ /2/ የእስካሁኑ የሥጋ ነበር አሁን ግን በነፍስ ትቀጣለህ።
  አይሻዳድ፡- በሊቀ ካህናቱ ፊት ጌታን በጥፊ መትቶታል በዚህም እጁ ደርቆ ሽባ ሆኖ ቀርቷል። ኦሪ
- አባቱ እስከዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ /17/ መጻፅን፣ ሌሎችን
- ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም /19/ ከአብ ተለይቼ ብቻዬን አንድም የአምላክነት ሥራ አልሠራም ሊል ነው።
- አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ወልድም ለሚወዳቸው ሐይወትን ይሰጣቸዋል ወልድ በአምላክነቱ ከአብ ጋር እኩል መሆኑን ያሳያል
- ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው /22/፡- አብ የማይፈርድ ሆኖ ሳይሆን ወልድ ሥጋን በመልበሱ የሚጠራጠሩ ሰዎች አሉና ፈራጅ መሆኑን ለመንገር
- ሌላው ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው ማት በሥጋ ተገልጦ፣ በፍጡራን ዓይን ታይቶ በአጋንንት የፈረደባቸው ለሰው ልጅ የፈረደላቸው እሱ
- ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል /25/ ሙታን የተባሉት በሥጋ የሞቱት አይደሉም ተስፋ የቆረጡት፣ የመዳን ሕልም የሌላቸው ኃጢአተኞች ናቸው። ወንጌልን የሚሰሙበት
  የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ግን፡- ወልደ መበለትን፣ አልአዛርን.....

Scanned with CamScanner

- በመ/ቃብር ያለ·ት· ሁሉ· ድሃሁን የሚሰመ·ዘት· ሰዓት· ያመሰገል /28/ ይህ ቃል ስለ ት·ንግሣኤ መ·ታ·ን ሲሆ·ን ዕለተ· ምጽአት·ን ያመለክ;ት·ል
- ለሕይወት· ት·ንግሣኤ፣ ለዓ·ርድ ት·ንግሣኤ /29/ አምነው· ተጠምቀው· ሥራ· የሠሩ·ና ያልሠሩ·.
- ስለኔ የሚመስነር ሌላ ነው· /32/፡- ስለእር·ሱ· የሚመስነሩ· 5 ምስነር·ች·
  1ኛ. ዮ·ሐ·ንስ /33/
  2ኛ. የሚሠራ·ው· አምላካዊ ሥራ· /36/
  3ኛ. የላከው· እግዚአብሔር አብ /37/
  4ኛ. ስለእር·ሱ· የተ·ጻፉ·ት· መጻሕፍ·ት· /39/
  5ኛ. ስለእር·ሱ· የጻፈ· መ·ሰ· /46/

Scanned with CamScanner

ስምንተኛ ሳምንት
ምዕራፍ ስድስት

ዮብርያዶስ በገሊላ ባሕር ምዕራባዊ ዳርቻ የሚገኝ ከተማ

- ጌታ ወደ ተራራ ጠባና ከደቀመዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ
  ተራራ፡- የልዕልና፣ የመንፈሳዊ ዕድገት፣ ወደ እግዚአብሔር የመትረብ ምልክት
  ተራራ፡- በብሉይ ኪዳን ብዙ ሃይማኖታዊ ሥራ ተሠርቶበታል
- የኃጥፈልጉኝ እንጀራን ስለበላችሁና ስለጠገባችሁ ነው /26/ ሕገበ ትኩረት የሰፈኩት ስለምድራዊው ነገር ብቻ ነበር ሊያነግሡት የፈለጉም በምድራዊ ኑሯቸው እንዲመቻቸው
- ሰሚጠፋ መብል አትሥሩ /27/፡- የሚሠፋ ያለው ያበረከተውን እንጀራ ነው
  - ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ማቴ፡4፥4
  - ወደ አፍ የሚገባ ወደ ሆድ አልፎ ወደ ውጪ ይጣላል ማቴ፡15፥17 ብሎ የዚህ ዓለም ምግብ የሚጠፋ መሆኑን
  - ቅዱስ ጳውሎስም መብል ለሆድ ነው፣ ሆድም ለመብል ነው እግዚአብሔር ግን ይህንንም ያጠፋዋል 1ኛ ቆሮ፡6፥13
  - ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ ለመብል አይደለም ዕብ፡13፥9
- እርሱን እግዚአብሔር አትሞታል /27/ ለዘለዓለም ሕይወት ለሚኖር መብል እንጂ ብሏቸው ነበርና አትሞታል ማለት አጽንኦታል ማለቱ ነው፡፡
  - በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ ኤፌ፡1፥13
  - ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ አንድም ኤፌ፡ 4፥30
  - የሚጠፋውን ምግብ ግን እግዚአብሔር አሳልፎታል
- ከሰማይ እንጀራ የሚሰጣችሁ አባቱ እንጂ ሙሴ አይደለም /32/ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ ብለው ከሙሴ ጋር አነጻጽረውት ነበርና
- የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለም ሕይወትን የሚሰጥ ነው፡፡ /33/
- የእግዚአብሔር እንጀራ የተባለ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡
- ይህን እንጀራ ስጠን ብለውት ከሰማይ የወረደ ሰማያዊ አምላክ መሆኑን
- የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም /35/ ልጅነትን ጽድቅንና ዘለዓለማዊ ሕይወትን፣ ሰላምንና ጸጋ መንፈስ ቅዱስን አይራብም፡፡ አንድ የተቀበሉት በኃጢአት ስላደፈ
- ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ስላላቸው አንጎራጎሩ /41/
  አይሁድ ሥጋዊ እንጀራን አበርክቶ ሲመግባቸው ሊያነግሡት ወደዱ፡፡ መንፈሳዊ እንጀራ ተመገቡ ባላቸው ጊዜ አንጎራጎሩ
- አባቱንና እናቱን የምናውቀው ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን /42/
  የአይሁድ ትልቁ ስህተት ወ/ዮሴፍ ነው ብለው ማመናቸው ነው፡፡ ጌታ እሱ ግን እኔንም ወይም አባቴንም አታውቁም ብሏቸዋል ዮሐ፡8፥19

Scanned with CamScanner

አያሁድ የርሱን ቃል ሠስማት ትተው የራሳቸውን ሀሳብ

- ሁሉም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማሩ ይሆናሉ /45/ ኢሳ፣54፥13፡- እግዚአብሔር ምሥጢር ይገልጥላቸዋል ማለት ነው። ኤር፣31፥34 ፣ ዕንባ፣2፥14
ምድር የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ትሞላለች
ሰብዲስ ኪዳን ምዕመናን ብዙ ምስጢር ተገልጧል

- አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም /49/ እስራኤልን ከሞት አላዳናቸውም ዘጸ፣16፥15
አሁን ከሰማይ የወረደው እንጀራ ግን ዘለዓለማዊ ሕይወትን የሚሰጥ ነው።

- ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው /54/ ዘለዓለማዊ ሕይወት በሥጋውና በደሙ እንደሚገኝ የብሉይ ኪዳንን መናና የሐዲስን እያዛመደ ይነግራቸዋል።

- እኔም በመጨረሻ ቀን አስነሣዋለሁ /54/ ማለቱ አስነስቶ ክብረ መንግሥተ ሰማያትን አወርሰዋለሁ ሲል ነው።

- ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው /55/፡- እውነተኛ የሚለው ሥጋው ደሙ ከዓለማዊ መብል መጠጥ የተለየ መሆኑን ያረጋግጣል
አባ ሕርያቆስም ኦ ማርያም በእንተዝ....

- የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል /57/፡- አብ ሕያው ስለሆነ ከአብ የተወለደ ወልድ ሕያው ነው። ወልድም ሕያው ስለሆነ የሱን ሥጋ የበላ ሕያው ይሆናል።
የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ለሚጠራጠሩት አምላክነቱን ለማስረዳት ነው ብለዋል።

- ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው /60/ ጌታ አንዳንድ ጊዜ ተሰምቶ የማያውቅ ይናገር ስለነበር ደቀመዛሙርቱ ተጠራጥረው ነው።

- የሰው ልጅ አስቀድሞ ወደነበረበት ሲወጣ ብታዩ እንዴት ይሆናል /62/ ሥጋውን ደሙን ከመስጠት ይልቅ ዕርገቱ ያስደንቃልና።

- ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው ሥጋ ምንም አይጠቅምም /63/ መንፈስ መለኮታዊ ሥልጣኑ ማዳን የሚችል መለኮት የተዋሐደው ሥጋ ነው እንጂ የዕሩቅ ብእሲ /የፍጡር/ ሥጋ ምንም አይጠቅምም።

- እኔ የነገርኳችሁ ቃል መንፈስ ነው /63/ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው ብሎ ነበርና የነገርኳችሁ ቃል የሕይወት ቃል ነው።

- ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደኋላ ተመለሱ /66/ ደቀመዛሙርት ያላቸው
1. ከሕዝቡ ወገን ብዙዎች
2. ሰባ አርድእት

- ጌታ ሆይ ወደማን እንሄዳለን /69/
አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንም አምነናል`በማለት የ12ቱን አሳብ በሊቀሐዋርያት በጴጥሮስ አንደበት ተገለጠ።

Scanned with CamScanner

ዘጠነኛ ሳምንት

ምዕራፍ ሰባት

- የአይሁድ የዳስ በዓል፡- 7 ቀን በአንድነት ይከበራል፡፡ ዘሌ፡23፥39-44 እስራኤል 40 ዘመን በምድረ በዳ መኖራቸውን ለማስታወስ ዳስ ሠርተው ያከብሩ ነበር፡፡
- የጌታ ወንድም የተባሉ ደቂቀ ዮሴፍ ናቸው፡፡ ማቴ፡12፥47፣ ማቴ፡13፥55፣ ማር፡3፥32፣ ሉቃ፡8፥20፣ ዮሐ፡2፥12
- ራስህን ለዓለም ግለጥ /4/፡- የግእዝ በግእዝ ራስን ግለጥ ያሉት ጌታ በሚያደርጋቸው ተአምራት ይመኩ ዘንድ ለራሳቸው ውዳሴ ከንቱ ሽተው ነው፡፡
- ጊዜዩ ገና አልደረሰም /6/ ለጊዜው ወደ በዓሉ የምወጣበት ሳይሆን ግን የምሰቀልበት ጊዜ አልደረሰም
- ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል /13/ ብዙዎቹ ምሁራነ ኦሪት ስለነበሩ እን ደነሱ ከምሁራኑ ሕገ ኦሪትን እየተማረ አላደገም እሱ ግን የእውቀቱ ሁሉ ባለቤት ጌታና ሳይማር ያስተምር ነበር፡፡ ጌታ ያደገ በተናቀችው በገሊላ ከተማ በናዝሬት ነው፡፡
- ትምህርቱ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም /16/ ሳይማር አዋቂ የሆነበትን ምሥጢር ነገራቸው፡፡
- ከእናንተ ሕግን የሚያደርግ እንድ ስንኳ የለም ስለምን ልትገሉኝ ትፈልጉኻላችሁ /19/ መሰ. ከጻፋቸው ሕጎች አንዱ ነፍስ አትግደል ነው፡፡ ዘጸ፡20፥13 እነሱ ግን እሱን ለመግደል ይፈልጋሉ፡፡
- ጋኔን አለብህ ማን ሊገልህ ይፈልጋል /20/ ሀሳባቸውን አውቆ ሲነግራቸው ጋኔን አለብህ አሉት፡፡ ከአጋንንት እነሱ ማቴ፡8፥28 ብለው
- መሰ. መገረዝን ሰጣችሁ /ጽፎ ስለሰጠ/ ከአባቶች ነው እንጂ ከመሰ. አይደለም /22/ ከአባቶች ማለት የተጀመረ በአብርሃም ጊዜ ስለሆነ ዘፍ፡17፥9-14
- በሰንበት ሰውን ትገርዛላችሁ /22/ መሰ ሕጻን በተወለደ በ8 ቀን ይገረዝ ብሎ ጽፏል፡፡ ዘሌ፡12፥3 በዚህ መሠረት ቅዳሜ የተወለደ 8ኛው ቀን ቅዳሜ ስለሚሆን ቅዳሜ ይገዘራል፡፡ የመሴን ህግ ለማክበር ቅዳሜ የምትገርዙ ከሆነ እኔ ድውይ ብፈውስ ለምት ትከሱኛላችሁ የማን ይበልጣል?
- ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ በመልክ አትፍረዱ /24/ በሰንበት በሰንበት መገዘርን ሳትቃወሙ በሽተኞችን ብፈውስ እኔን መቃወማችሁ
- እናንተ የማታውቁት የላከኝ እውነተኛ ነው /28/ እናውቀዋለን የሚሉትን አብን ሉን ያህል እንደማያውቁት እና የዮሴፍ ልጅ እንዳልሆነ
- ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም እጁን አልጫነበትም /30/ ጌታ የሚያዝ ፈሪሳውያን ሊገሉት ባሰቡበት ሳይሆን ቀኑ ሲደርስ
- እኔ ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም /34/ ለሐዋርያት እሱ ሊሰቀል አብረውት እንደማይሞቱ
- አይሁድን ግን እኔ ወደማወርሳት መንግሥቱ ለማያት አትገቡም

Scanned with CamScanner

- የግሪክን ሰዎች ሊያስተምር አለውን /35/፡- አስራኤል ከባቢሎን ምርኮ ከተመለሰ ብኃላ በአሕዛብ አገር ሁሉ ተበትነው ይኖሩ ነበርና እኛ ወደማንሄድበት ሃገር ሄዶ የተበተኑትን አይሁድ ሊያስተምር ነውን? አሉ ስላልገባቸው
- ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ /37/ ከብርን፣ ልጅነትን፣ ሕይወትን የሚሻ ቢኖር ማለቱ ነው።
- የሕይወት ውኃን ከሰዱ ይፈልቃል /38/ ምዕ 4 ቁጥር 10 ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። የሕይወት ውኃን የተባለ ሐዋርያት ምዕመናን የሚቀበሉት ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ነወ።
- ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ቅዱስ ገና አልወረደም ነበርና /39/ ይኸ ማለት፡- ስላልተሰቀለ ስላልሞተ ማለት ነው።
- ክርስቶስ በውኑ ከገሊላ ይመጣልን /42/ ይሀን ያሉ ጌታ ከገሊላ አይወጣም ብለው የሚያምኑ አይሁድ ናቸው። እስራኤል ገሊላን ይንቋት ነበር ምክንያቱ ድግሞ ለእስራኤል ሀገሮች ጠረፍ በመሆኗና አሕዛብ ሰፍረውባት ስለሚኖሩ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ገጽ 125 ላይ
- የመልእክተኞቹ ምስክርነት፡- እንደዚህ ሰው ማንም ከቶ አልተናገረም /46/ መያዝ፣ መወቀስ የለበትም ማለታቸው ነው።
- የኒቆዲሞስ ምስክርነት፡- ሕጋችን ከሱ ሳይሰማ ምንስ እንዳደረገ ሳያውት በለው ይፈርዳልን /50/ ምሁረ አራት፣ ሕግ አዋቂ ስለሆነ

ሕጋቸው፡- ንጹሐንና ጻድቃን አትግደል ዘጸ፡23፡7 ተብሏል ማ

ማር ዮሐንስ፡- ኒቆዲሞስ እንዲህ በማለቱ ከአለቆች ወይስ ከፈሪሳውያን በእርሱ ያመነ አለን ያሉትን አፈረሰባቸው ብሏል።

ሲያስተምር ውሉ ወደ ደብረ ዘይት ሄዶ አድሮ ወደ መቅደስ መጥቶ ያስተምራቸው ጀመር።

Scanned with CamScanner

አስረኛ ሳምንት

ምዕራፍ ስምንት

- በምንገዘር የተያዘች ሴት ወደሰ አመጠሙለት /3/ ለመፈተን ፈራሳውያንን ያሳሰባቸው የገዘሙት ኃጢአት መሠራት አይደለም ሕጉም የሚለው ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ቢያመነዝር ሁለቱም ፈጽመው ይገደሉ። ዘሌ፣20፥10፣ ዘዳ፣22፥22
- ጎንበስ ብሎ በጣት በምድር ላይ ጻፈ /6/ የጻፈው ኃጢአታቸውን ነው። እሱ በምድር ላይ ሲጽፍ በአእምሮአቸው እንዲያስታውሱት አደረጋቸው። በጎደኛቸው ግንባር ተጽፏል፣
- ከላይኛኛሽ ወደየት አሉ ሴላት አላውቅም /10/ ማለት የኔን ኃጢአተኛነት እንጂ ሆነሱን አላውቅም አለችው። እኔም አልፈርድብሽም ደግመሽ ኃጢአት አትስሪ /11/ የባለ እንዳያገኝሽ እንደ መጻጉዕ
- የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም /12/፡- ብርሃን የእምነት፣ የእውቀት፣ የጽድቅ ምሳሌ ነው።
- እናንተ ሥጋዊ ፍርድን ትፈርዳላችሁ /15/ የራሳቸውን ሰውረው አመንገራጉ እንድትሞት ፈርደዋልና።
- እኔንም አባቴንም አታውቁም /19/፡- እኔ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኔን እግዚአብሔር አብም የእኔ አባት መሆኑን ስለማታውቁ ወልደ ዮሴፍ ትሉኛላችሁ።
- እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም /21/ አይሁድ እንደማይድኑ ሲነግራቸው ነው።
- በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ /21/ ሞት ማለት የናጡራን ሕይወት ከሰጠው ከእግዚአብሔር መለየት ከኃጢአታቸው በመሞታቸው
- እናንተ ከታች ናችሁ እኔ ከላይ ነኝ /23/፡- ሰማያዊ አምላክ እግዚአብሔር መሆኑን ሲነግራቸው
- የሰውን ልጅ ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ /28/ ፡- በሰቀላችሁት ጊዜ
- እውነት አርነት ያወጣችኋል /32/፡- ከዚህ በፊት ዲያቢሎስ በሀሰት የሰው ልጆችን አምላክ ትሆናላችሁ ብሎ ለባርነት ዳርጓቸው ስለነበር አሁን ጌታ በእውነት ነጻ ያወጣቸዋል።
- ለማንም ከቶ ባሮች አልሆንም /33/፡- በግብጻውያን 215 በባቢሎናውያን 70 ዘመን የተገዙትን ዘንግተው 2ኛ ነገ፡25፥8፣ 2ኛ ዜና፡36፥17
  በዚያም ዘመን ከቁሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ሲሉ ዮሐ፡19፥15
- ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው /34/ ሌላው ቢቀር ኃጢአት እየሠራችሁ ስለሆነ የኃጢአት ባሪያዎች ናችሁ።
- በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ /38/፡- አባት ዲያቢሎስ
- የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር /39/
  አብርሃም እንዲህ አላደረገም
- እኛ ከገሙት አልተወለድንም /41/፡- በገሙት ከአጋር ፣ ከተወለደው ከእስማኤል አልተወለድንም ማለታቸው
- ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘለዓለም ሞትን አይቀምስም /51/

Scanned with CamScanner

1. በሞት ይነሣል
2. ሞተ ነፍስ አያገኘውም

- አብርሃም ተኒን ያደ ዘንድ ተመኘ አየም ደስም አለው /56/
  1. በእምነት በሰጠው ቃል ከጸን
  2. መልከጼዴቅን አግኙ ህብስት
- አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ /59/፡- ቀዳማዊነቱን የባሕርይ አምላክነቱን ገልጾ ነገራቸው።
- ፈሪሳዊ አብን እሳየንና ይበቃናል /8/ አብን ለማወቅ ያቀረበው ጥያቄ ጌታን በሰው ነት እንጂ በመለኮታዊ ባሕርይው እንደማያውቀው ገለጸለት
- ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝም /9/ አንድነታቸው አታውቁኝም ማለቱ የአብ ሥልጣን የእኔ ሥልጣን የአብ መንግሥት የኔ መንግሥት ነው ሊለው
  - ❖ የግእዝ በግእዝ፡- ፊልጶስ ወልድን በአምላክነቱ አውቆት ቢሆን አብን አሳየን ብሎ አይጠይቀውም ነበር ብለዋል።
- እኔን ያየ አብን አየ /9/ ማለት በኔ ሀልው ሆኖ በሚያደርገው ታምራት አምላክነቱን ይገልጣል ማለቱ ነው እንጂ በሥጋ አብ አልተገለጠም።
  - ❖ የግእዝ በግእዝ፡- እኔን ያወቀ አብን ያውቀዋል ማለቱ ነው።
- እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን /10/ ከጌታ በፊት ይህን ትምህርት ያስተማረ ነቢይ ወይም ሐዋርያ የለም።
- በኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል /12/ ጌታ ካረገ በኃላ ሐዋርያት ጌታ ያደረገውን ሁሉ አድርገዋል።
- ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል /12/ የበለጠ አድርገው ሳይሆን እሱ ካደረገው የበዛ ብዙ ዘመን ስላደረገ ነው። ብዙ ዘመን፣ በብዙ ቦታ፣ ብዙ ታምራት ስላደረገ እሱ 3 ዓመት
- እኔም አብን እለምናለሁ ሌላ አጽናኝ ይለጣችኋል /15/ በዚህ ምዕራፍ ወልድ አብን እንደሚለምንና መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት እንደሚሰጥ ቢገልጽም ምዕ፡16፣7 ላይ ወልድ ራሱ እንደሚልከው ተገልጿል።
  - ❖ አብ ይለጣችኋል፣ እኔ እልከዋለሁ ማለት መንፈስ ቅዱስ ወደ ሐዋርያት የሚመጣው በአብ፣ በወልድ ፈቃድ ዘራሱ ፈቃድ ነውና።
- ሌላ አጽናኝ /16/ በአካል ልዩ መሆኑን ያመለክታል። 3 አካላት እንዳለ ገለጸ እኔ አብን እለምናለሁ ሌላ አጽናኝ ብሎ
  - ❖ ጸራቅሊጦስ ቃሉ የጽርዕ ነው። በግዕዝ ከሣቲ፣ ናዛዚ፣ መጽንዒ፣ መንጽሐ፣ መስተሥርዩ፣ መስተፍስሒ ማለት ነው።
- ዓለም ሊቀበለው የማይችለው /17/ ዓለም ያለው በሃይማኖት በጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ልጅ ያልሆነ ሰው ሁሉ ነው።
- ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም /18/ እሄዳለሁ ብሏቸው ነበርና ብቸኝነት እንዳይሰማቸው አልተዋችሁም።

Scanned with CamScanner

❖ የግእዝ በግእዝ መተርጉማን፡- ገዛኒ በእንተ ተድላ ሥለሞ" በሚልው ለጻድቃን በመወርዊሠመ ማለት ለጻድቃን በየመወረታቸው የተዘጋጀ የወዲያኛው ሥለሞ" ነው ብሎ ተርጉመዋል።

Scanned with CamScanner

አስራ አንደኛ ሳምንት

ምዕራፍ 10

- ❖ አንተም አባግዕሰ በመጣል ይታወቃል።
- ❖ ቤተክርስቲያን፡ ጠባቂ፣ ተጠባቂ፣ አስጠባቂ ናት።
- ❖ የእረኛው ድርሻ፡- በበሩ ከመግባት - ነፍሱን ለበጎች ምእመናን በጎች
- ❖ የመንጋው ድርሻ፡- እረኛውን ከማወቅ እስከ መከተል

- በጎች፡- ምእመናን ናቸው /ማቴ፡25፡33/ በጎቹን በተኙ በጎች ያለጠባቂ መኖር አይችሉም፡፡ ምእመናንም ያለ ክርስቶስ ጠባቂነት መኖር አይችሉም፡፡
- በረት፡- በጎችና ሌሎች እንስሳት የሚያድሩበት ቤት ነው፡፡ በዚህ የተመሰለች ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡
  - ❖ የበጎች ማደሪያ በረት እንደሆነ የምእመናንም መኖሪያ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡
- በበሩ የማይገባ፡- ሌባ፣ ቀማኛ፣ ወንበዴ ምንጊዜም በበር አይገባም፡፡ ትክክለኛውን የማስተማር መንገድ፣ እውነተኛውን የወንጌል ትምህርት የማያስተምር ሰው ወይም በክርስቶስ ስም የሚመጣው ሐ/ቁ
- በበሩ የሚገባ የበጎች እረኛ ነው፡- በበር የሚገባ ባለቤት ወይም እንዲገባ የተፈቀደለት ሰው ነው፡፡ ወደ በረትም የሚገባም ጠባቂ ወይም ባለቤት
  - ❖ በር የተባለ ነቢያት የተናገሩት ትንቢት፣ የቆጠሩት ሱባኤ ነው፡፡
  - ❖ በበሩ የሚገባ የተባለ ትንቢተ ነቢያትን የፈጸመ፣ እውነተኛ ጠባቂ / እረኛ
  - ❖ ሌላው በበሩ የሚገባ የተባለ፡- ጌታ ያስተማረውን ትምህርት በትክክል የሚያስተምር መምህር ወይም ሐዋር ነው፡፡
- በረኛው ይከፍትለታል /ለጌታ/ /3/ በረኛ ማለት በበሩ ላይ ሥልጣን ያለው የሚዘጋና የሚከፍት እረኛው /ባለቤቱ/ ሲመጣ ይከፍታል፡፡
- በረኛው ይከፍትለታል ማለት እግዚአብሔር አብ ይመለክርለታል፣ ዮሐንስ መንገድ ይጠርግለታል፣ ነቢያት ትንቢት ይናገሩለታል፡፡
- ሌላው ለእውነተኛው ሐዋርያ መንፈስ ቅዱስ ምስጢሩን ይገልጽለታል፡፡
- በጎቹን በየስማቸው ይጠራቸዋል /3/ በግ ጠባቂ ለበጎቹ ስም ያወጣል፡፡ መልካቸውን፣ አካላቸውን፣ ቀለማቸውን በሚገልጥ ሁኔታ ቀንዲት፣ ሶሪት
- ጌታም ደቀመዛሙርቱን ሐዋርያት፣ ሰብአ አርድእት እያለ ብቻ ሳይሆን ከሐዋርያትም በሌላ ስም የጠራቸው አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ስምዖንን ጴጥሮስ፣ ዲዲሞስን ቶማስ፣ ልብድዮስን ታዴዎስ ወዘተ..
- ዛሬም ምእመናን ሲጠመቁ የጌታን ስያሜ መሠረት በማድረግ ወንዶችን ገብረሥላሴ፣ ወ/ሥላሴ፣ ገብረኢየሱስ፣ ገብረ ክርስቶስ ሴቶችንም ወለተ ሥላሴ፣ አመተሥላሴ፣ ወለተ ክርስቶስ፣ አመተ ኢየሱስ እየተባሉ ይሰየማሉ፡፡
- በፊታቸው ይሄዳል /4/ አጠባበቅ በየሀገሩ ቢለያይም ለምሳሌው የሚመች በፊት ሲኬድ ስለሆነ

Scanned with CamScanner

- ጌታም ለምእመናን በፈታቸው ይሄዳል ማለት፡- ምእመናን የሚሠሩትን ሥርዐቱ ያሳያቸዋል፡፡ ተጠምቆ ጥምቀትን፣ ጸሎ ጾምን ጠዘተ
- በፈታቸው ይሄዳል፡- ማለት ለምእመናን ተላልፎ ይሞታል፡፡
- በጎች ድምፁን አውቀው ይከተሉታል /4/ በጎች የጠባቂያቸውን መይም የባለቤታቸውን ድምፅ ለይተው ያውቃሉ፡፡ በተለይ እንስሳት በሙሉ የሚያድሩበትን፣ የሚመገቡትንና ውኃ የሚጠጡበትን ቦታ ለይተው ያውቃሉ፡፡ ኢሳ፡1፥3 በሬ የገዣውን፣ አህያም የጌታውን ጋጣ አወቀ፡፡ እንደዚሁም ሁሉ ምእመናን የጌታን ቃል መንጌሉን ትምህርት ማወቅ አለባቸው፡፡
- ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አያከተሉትም /5/ እኔ ክርስቶስ ነኝ ብሎ የሚመጣውን ሁሉ መከተል የለባቸውም፡፡
- እኔ የበጎች በር ነኝ /7/ ማለት ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ በኢየሱስ ክርስቶስ /በኔ/ የባሕርይ አምላክነት አምነው
- ከኔ በፊት የመጡ ሌቦች ወንበዴዎች ናቸው /8/ ግብ.ሐዋርያት ምዕ፡5፥33-39 ገማልያል ታሪካቸውን የገለጣቸው ይሁዳ ዘገሊላ እና ቴዎዳስ ዘግብዕ
- በኔ የሚገባ ይድናል /9/ በኔ አምኖ ተጠምቆ ሥራ የሚሠራ ይገባልም ይወጣልም /9/ ይገባል ወደ ሃይማኖት ወደ ክርስትና ይወጣል ማለት መከራ ለመቀበል ማለት ነው ፡፡
- መሰማርያ ያገኛል /9/ ማለት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምኖ መከራ የሚቀበል ኡማኝ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚያገኝባት መንግሥተ ሰማያት
- መልካም እረኛ ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ /11/ እረኝነት በብሉይ ኪዳን ሲአስተም ኖነበሩ ካህናት፣ ትንቢት የተናገሩ ነቢያት እረኞች ጠባቂዎች ተብለዋል ሕዝ፡3፥17 ሕዝክ፡34፥2-6
- እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የሾማቸው ነገሥታት እረኞች ይላቸዋል፡፡ ኢሳ፡44፥28፣ ዘካር፡11፥15-17፣ ኤር፡51፥23 ወዘተ...
- ጌታ መልካም እረኛ እኔ ነኝ ብሎ ከማስተማሩ በፊት በብሉይ ኪዳን ኤራሉ እግዚአብሔር የሕዝቡ እረኛ እንደሆነና ሕዝቡን እንደሚጠብቅ ተናግሯል፡፡ መዝ 22፡1፡- እግዚአብሔር እረኛዬ ኢሳ፡40፥11፡፡ መንጋውን እንደ እረኛ ያስማራል፡፡ ኤር፡31፥10፣ 2ኛ ሳሙ፡22፥3፥47 እግዚአብሔር ጠባቂዬ ነው፡፡ መዝ፡79፥1 የእስራኤል ጠባቂ ሆይ አድምጥ፡፡ ኢሳ፡27፥3 እኔ እግዚአብሔር ጠባቂ ነኝ፡፡
- አሁንም እንዲህ ማለቱ በብሉይ ኪዳን ሕዝቤን ስጠብቅ የነበርኩ አምላክ በሐዲስ ኪዳን በሥጋ ተገልጬ ሕዝቤን ልጠብቅ መጥቻለሁ ማለቱ ነው፡፡
- በሐዲስ ኪዳን ቅዱስ ጳውሎስ ዕብ፡13፥20፣ 1ኛ ጴጥ፡2፥25፣ ራዕ፡7፥17
    - ❖ በዘለዓለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችን ኢየሱስን
    - ❖ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል
    - ❖ በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና ወደ ሕይወት ውኃ ይመራቸዋል፡፡
- ማር.ዮሐንስ፡- ራሱን አንድ ጊዜ በግ፣ አንድ ጊዜ እረኛ ማለቱ እረኛ ማለቱ ወደ ጽድቅ ሁሉ ስለመራን በግ ማለቱ መሥዋዕት ስለሆነልን ነው ብሏል፡፡

Scanned with CamScanner

- መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል /11/ ብዙዎች በጎቹን የሚበዘብዙ ለራሳቸው ነጥቅም ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለምእመናን ቤዛ ሆኖ ሞቷል። እንኳን በጎቹን ሸሽቶ ሊበላ ራሱ በ30 ብር ተሸጦ በደም ዋጋ ምእመናንን የሚገዛ እረኛ ነው።
- መልካም እረኛ መባል ይገባዋል።
    - ❖ በበጎቹ የሚበለጽግ ሳይሆን በጎቹን የሚያበለጽግ
    - ❖ በጎቹን የሚያስር ሳይሆን ስለ በጎቹ የታሰረ
    - ❖ በጎቹን ለመስዋዕት የሚያቀርብ ሳይሆን ራሱ መስዋዕት የሆነ
- ሚያሌኖ/ ምንደኛ /12/ ተቀጣሪ ማለት ነው። ተከላ በመጣ ጊዜ ከበጎቹ ሕይወት ይልቅ ለራሱ ቅድሚያ የሚሰጥ
- ሞያተኛ/ ምንደኛ የተባሉ በሕገበ ላይ የተሾመ ግዴለሽ /ቸልተኛ/ አገልጋዮች ፣ተከላ የተባሉ ከሃዲያን፣ መናፍቃን፣ ምእመናንን ከቤተ ክርስቲያን እየነጠቁ ሊወስዷቸው አይከላከሉም።
- ምእመናንን ስለመጠበቅ መነቀፍ፣ መሰደብ፣ መደብደብ፣ መገደል አይፈልጉም፣ ራሳቸውን ያድናሉ እንጂ።
- ከዚህ በፊት ያልሆኑ ሌሎች በጎች /16/፡- በረት የተባለች ኢየሩሳሌም ስለዚህ ከእስራኤል ውጪ በሌላው ዓለም የሚኖሩ አሕዛብ/ ምእመናን ማለቱ ነው።
    - ❖ አይሻዳድ፡- ያምኑበት ዘንድ ስላላቸው አሕዛብ አንድ እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
- አንድ መንጋ፣ እረኛውም አንድ /16/ አካል፣ ብልት፣ ማህበር፣ ቤተሰብ
- በፈቃዴ አኖራታለሁ ከእኔ ማንም አይወስዳትም /18/፡- ነፍሱን ለመከራ አሳልፎ የሚሰጥ በፈቃዱ ነፍሱን ከሥጋው የሚለይ በፈቃዱ መሆኑን
- ሥልጣን አለኝ ማለቱ በ3ኛው ቀን ነፍሱን ከሥጋው ጋር አዋሕዶ የማስነሳት ሥልጣን የባሕርይው እንደሆነ
- የመቅደስ መታደስ በዓል /22/ ሊቀካህናቱ አልዓዛር አይሁድን ሲመራ የጽርዕ ሰው አንጥያኮስ ነቢይት ሀልዳና ከዚያ በኋላ ቤተመቅደሱ የታደሰበት በዓል ታህሣሥ 8 ቀን በየዓመቱ ይከበር ስለነበር
- በሰሎሞን ደጅ መመላለሻ /23/ ወደ ቤተመቅደሱ የሚወጣበት ደረጃ ሰሎሞን የሠራውን ታላቁን ቤተመቅደስ ባቢሎናውን አቃጥለውታል። 2ኛ.ነገ፡25፥9
- ጌታ የተመላለሰው በዘሩባቤል ጊዜ በተሠራው ቤተመቅደስ ነው። እንዴት እንደተሠራ ዮሐ፡2፥20 ላይ ያለው ታሪክ ነው።
- የሰሎሞን መመላለሻ የተባለው ሰሎሞን እንደሠራው ተደርጎ ስለተሠራና በሰሎሞን ስም ስለተጠራ ነው።
- የአብ ልጅ ነው ወይስ የዮሴፍ? ፍጡር ነው ፈጣሪ? እስከመቼ ድረስ በጥርጣሬ ታቆየናለህ ብለውት ነበርና
- እኔና አብ አንድ ነን /30/ በባሕርይ፣ በሥልጣን፣ በአምላክነት
- እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ /34/፡- ቃሉ የዳዊት ነው መዝ፡82፥6
  ይህ ቃል ሁለት ነገሮችን ይገልጻል።

Scanned with CamScanner

አስራ ሁለተኛ ሳምንት

ምዕራፍ 11

ስለአልአዛር መታመምና መሞት

- ቤታንያ፡- ከኢየሩሳሌም በስተምስራት 5 ኪ.ሎ- ሜትር
- ማርያምና ማርታ፡- በጌታ ያመኑ ሉቃ፣10፥38-42
- የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ /4/ ይህ ህመም ለሞት አይደለም፡፡
- ጌታ ማርታንና እህቷን አልዓዛርን ይወድ ነበር /5/ በሃማይኖታቸው በምግባራቸው
- በነበረበት ቦታ ሁለት ቀን ሞለ /6/ ጌታ የሰማ ረቡዕ ነው የሞተም ረቡዕ ነው ግ-ዳሜ አስነስቶታል፡፡
- ቀኑ 12 ሰዓት አይደለምን /9/ ቀኑ ሳያልፍ ሌሊቱ እንዳይመጣ ጊዜው ሳይያረስ አልሞትም ሲል ነው
- በቀን የሚመላለስ አይሰናከልም /9/ ብርሃን አኔ እያለሁ አይገሏችሁም፡፡
- አይሻዳድ፡- ቀን የሚለው ትምህርቱን ዕውቀቱን የደቀመዛሙርቱን የአእምሮ መጨ.ለም ነው ብሏል፡፡
- በሌሊት የሚመላለስ /10/ በክህደት በድንቁርና....
- ከእንቅልፍ ላስነሣው እሄዳለሁ /11/ ሞትን እንቅልፍ ሲል ነው፡፡ ማንቀላፋታችን፣ መሞታችን፣ መንቃታችን ደግሞ ትንሣኤያችን ነውና፡፡ ዳዊት ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፡፡ 1ኛ.ነገ፡2፥10፣ 1ኛ.ነገ፡11፥43፣ 14፥31
- ባለመኖሬ ስለእናንተ ደስ ይለኛል /15/ በቦታው ሳይኖር ማወቁ አምላክ ቢሆን ነው፡፡
- ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ /25/ ማስነሳት እንደሚችል
- የሚያምንብኝ ለዘለዓለም አይሞትም /26/ ሞቱ ጊዜያዊ ሕይወቱ ግን ዘለዓለማዊ ይሆናል ሲል ሲል ነው፡፡
- በመንፈሱ አዘነ /33/ ማር.ዮሐንስ ፍጹም ሰው መሆኑን፣ ጽንዓ ፍቅሩን ለመግለጽ፣ ከሚያገኑት ጋር አብረን ማዘን እንዳለብን
- ወዴት ቀበራችሁት /34/ አላዋቂ ሥጋን እንደተዋሐደ አይቱ ሀሰ-ከ አዳም ብሎ- የጠየቀ ቀዳማዊ አምላክ
- ዓይኖቹን ወደላይ አነሣ /41/ ሥርዓተ ጸሎትን ሲያስተምር፣ ተአምራት ይደረግልን ባላችሁ ጊዜ ጸልዩ
- የቀያፋ ትንቢት /49/

Scanned with CamScanner

አስራ ሦስተኛ ሳምንት

ምዕራፍ 12

ከፋሲካ በፊት በ6ኛው ቀን ወደ ቢታንያ መጣ ቢታንያ ከኢየሩሳሌም በሰተምስራት 5 ኪሎ ሜትር

- በዚያ እራት አደረጉለት ማርታ ታገለግል ነበር።
- ማርያም ሽቱ እግሩን ቀባች የቀቡት ሁለት ናቸው።
  1ኛ. ሉቃ፡7፥36 እና ስንክሳር የካቲት 6 ቀን ማርያም ኃጥዕት
  2ኛ. የአልዓዛር እህት
- ጌታ ኢየሱስ ከክበረ በኋላ /16/ ከተሰቀለ በኋላ በሞቱ እኛ ከብረንበታልና።
- የግሪክ ሰዎች /20/ 1ኛ. በእስራኤል ሃይማኖት አምነው በዓሉን ለማክበር የመጡ
  2ኛ. ስነ በዓል ለማየት የመጡ ግሪካውያን ናቸው።
- የስንዴ ቅንጣት /24/ ተዘርታ በስብሳ ብዙ ፍሬ .... በጌታ ሞት ብዙ መታን ህያዋን ይሆናሉና።
- ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል /25/ በሰውነቱ መከራ የሚቀበል ማለት ነው።
- አባት ሆይ ከዚህ ሰዓት አድነኝ /27/ ብሎ መጸለዩ
  1. ይህች የሞት ጽዋዕ /መከራ/ ከምእመናን ትሰፍ
  2. ለጸሎት አርአያ ለመሆን
- ልጅህን አክብረው /28/ አምላክነቱን ግለጸው
- የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል /31/ ዲያብሎስ ድል መሆኑን
- ከፍ ከፍ ስል ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ /32/ በተሰቀልክ ጊዜ
- ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ /35/ 1ኛ. ጌታ ነው 2ኛ. ብርሃን እድሚያችሁ
- የእግዚአብሔር ክንድ ለማን ተገለጠ /38/ የተባለ ጌታ ነው
- ዓለምን ላድን እንጂ በዓለሙ ልፈርድ አልመጣሁም /47/ ለሚያምን ሁሉ
- የተናገርኩት ቃል በመጨረሻ ቀን ይፈርድበታል /48/
- በመጨረሻ፡- መጸሕፍት ይትከሰታ ለስም ቅዱስ ያሬድ
  - ❖ የሕይወት ቃል ተከፈተ። ራእ፡20፥12

Scanned with CamScanner

- ነፍሰጡን ሰንካ ስለ አንተ አሰላለሁ /38/ ጽንሱ ሳትሩን ነገረው እንጂ ልትከ-ሥላኝ አትችልም ብሎት ነበር።
- ሦስት ጊዜ እስክትክደኝ ድረስ ዶሮ አያጮህም /38/
4፡፱ም ወንጌላውያን ጽፈዋል።

Scanned with CamScanner

አስራ አምስተኛ ሳምንት

ምዕራፍ 14

- ልባችሁ አይታወክ /1/ የማያምን አይረጋገም
  - በእግዚአብሔር ያመነ ለው አይታወክምና።
- በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ /2/ የአባቴ ቤት መንግሥት ለማያት ናት በብዙ ቋንቋን ትጠረላለችና።
- ስላንተ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ /2/ የተፈጠረች ዓለም ሳይፈጠር ሆኖ ሳለ ሌላ ዓለም እንዳለ ደቀመዛሙርቱ እንዲረዱ ተስፋ እንዲል
- ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ /3/ ዳግም ምጽአቱን ሲያስረዳ "አብረን መከራ ብንቀበል አብረን ወራሾች ነን" ሮሜ 8፥17
- የምሄድበትን አታውቁም መንገዱን ግን ታውቃላችሁ /4/ ማለት አብን አታውቁም፣ እኔን ግን ታውቁኛላችሁ።
- እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ /6/
- መንገድ 1. ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገርን በእሱ ነውና
  2. በሥጋ ተገልጦ ባደረጋቸው ተአምራት አምላክነቱን ወደ ማወት አድርሶናልና
  3. አንካሶች፣ ሽባዎች፣ የሚሮጡበት መንገድ
- እውነት፡- የእግዚአብሔር ልጅ ማለቱ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ፣ ብርሃን ነኝ፣ መልካም እረኛ ነኝ ማለቱ ስለሆነ
- ሕይወት፡- ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ሕይወት የምሰጥ እኔ ነኝ
- ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም /6/ በኔ ሳያምን በአብ ማመን የሚቻለው የለም። አይሁድ በአብ አምነን ብቻ እንድናለን ብለውት ስለነበር
- በወልድ ያመነ የዘለዓለም ሕይወት አለው ስለሆነ ነው
- አብን አሳየንና ይበቃናል /8/ እኔን ያየ አብን አይታል /8፣9/ በህልውና አንድ ናቸውና
- በኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ከዚህም የሚበልጥ የደርጋል /12/ ብዙ ዘመን በዓለም ሁሉ
- በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርጋለሁ /13/ በስሙ አጋንንትን አውጥተዋል። በስሜ አምናችሁ
- እኔም አብን እለምናለሁ /15/ ጸሎትን ለሐዋርያት ለማስተማር፣ ፍጹም ለው
- ሌላ አጽናኝ ጸራቅሊጦስ /16/ የእውነት መንፈስ፡- ከሣቲ፣ ናዛዚ፣ መጽንዓ፣ መንጽሐ
- ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች /18/
- ወደርሱ እንመጣለን በርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን /23/ በረድኤት፣ በጸጋ
- ፊልጶስ አብን አሳየንና ይበቃናል /8/ አብን ለማወቅ ያቀረበው ጥያቄ ጌታን በለውነቱ እንጂ በመለኮታዊ ባሕርይው እንደማያውቀው ገለጸለት
- ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን /9/ ,አንድነታቸው አታውቀኝም ማለቱ የአብ ሥልጣን የእኔ ሥልጣን የአብ መንግሥት የኔ መንግሥት ነው ሊለው

Scanned with CamScanner

❖ የግእዝ በግእዝ፡- ፊልጶስ ወልድን በአምላክነቱ አወቁት ቢሆን አብን አሳየን ብሎ አያጠይቀውም ነበረ ብለዋል፡፡

- እኔን ያየ አብን አየ /9/ ማለት በኔ ሀልው ሆኖ በሚያደርገው ታምራት አምላክ ነቱን ይገልጣል ማለቱ ነው እንጂ በሥጋ አብ አልተገለጠም፡፡

❖ የግእዝ በግእዝ፡- እኔን ያወቀ አብን ያወቀዋል ማለቱ ነው፡፡

- እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን /10/ ከጌታ በፊት ይሆን ትምህርት ያስተማረ ነቢይ ወይም ሐዋርያ የለም፡፡
- በኔ ላይ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል /12/ ጌታ ካረገ ጠንላ ሐዋርያት ጌታ ያደረገውን ሁሉ አድርገዋል፡፡
- ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል /12/ የበለጠ አድርገው ሳይሆን እሱ ካደረገው የበዛ ብዙ ዘመን ስላደረጉ ነው፡፡ ብዙ ዘመን፣ በብዙ ቦታ፣ ብዙ ታምራት ስላደረጉ እሱ 3 ዓመት
- እኔም አብን እለምናለሁ ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል /15/ በዚህ ምዕራፍ ወልድ አብን እንደሚለምንና መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት እንደሚሰጥ በገለጸም ምዕ፡16፡7 ላይ መልድ ራሱ እንደሚልከው ተገልጿል፡፡

❖ አብ ይሰጣችኋል፣ እኔ እልክዋለሁ ማለት መንፈስ ቅዱስ ወደ ሐዋርያት የሚመጣው በአብ፣ በወልድ ፈቃድ በራሱ ፈቃድ ነውና፡፡

- ሌላ አጽናኝ /16/ በአካል ልዩ መሆኑን ያመለክታል፡፡ 3 አካላት እንዳለ ገለጸ እኔ አብን እለምናለሁ ሌላ አጽናኝ ብሎ

❖ ጸራቅሊጦስ ቃሉ የጽርዕ ነው፡፡ በገዕዝ ከሣቲ፣ ናዛዚ፣ መጽንዓ፣ መንጽሐ፣ መስተሥርዮ፣ መስተፍስሐ ማለት ነው፡፡

- ዓለም ሊቀበለው የማይችለው /17/ ዓለም ያለው በሃይማኖት በጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ልጅ ያልሆነ ሰው ሁሉ ነው፡፡
- ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም /18/ እሄዳለሁ ብሏቸው ነበርና ብቸኝነት እንዳይሰማቸው አልተዋችሁም፡፡

❖ የግእዝ በግእዝ መተርጉማን፡- ገዚ በእንተ ተድላ ዓለም ዘጽልው ለጻድቃን በበመዐርጊሆሙ ማለት ለጻድቃን በየመዐረጋቸው የተዘጋጀ የወዲያኛው ዓለም ክብር ነው ብለው ተርጉመዋል፡፡

Scanned with CamScanner

አስራ ስድስተኛ ሳምንት

ምዕራፍ 15

እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፡- ከሞንት ጆምሮ የታጠቀ

ዘፍ፡14፥18 | ዘፍ፡13፥23 | ዘካ፡49፥11 — ውርንጫውን በወይን ግንድ ያሰረ ልብሱን በወይን ያጥባል ቅዱስ ያሬድም ባርከኮ ያዕቆብ ለይሁዳ ወልዱ ወይቤሉ- ንገሥ ዘይመጽእ እምኒከ ዘየሐጽብ በወይን ልብሰ ጠበጸመ አስካል ሰንዱኖ ንገሦ፡ ለእስራኤል

- ❖ በብሉይ ኪዳን ወይን ለቁርባን ይሆን ነበር፡፡ ዘጸ፡29፥40
- ❖ በብሉይ ኪዳን ወይን የሰው ልብ ደስ ያሰኛል፡፡ መዝ፡103፥15፣ ሚሳ፡31፥6፣ መክ፡10፥19
- ❖ ከአትክልት ሁሉ የተመረጠ ተክል ነው፡፡
- ❖ ተካዩ- ኢሳ፡55፥1 ኑ ያለ ዋጋ የወይን ጠጅ ግዙ ይላል፡፡

- ገበሬውም አባቱ ነው፡- የወይን ተክል የሚንከባከበው ያስፈልገዋል፡፡ ወልድም በአባቡ ፈቃድ ሰው ሆኗልና፡፡
- ፍሬ የማያፈራውን ቅርንጫፍ ያስወግደዋል /2/ አምኖ፣ ተጠምቆ ሥራ የማይሠራውን ይፈርድበታል፡፡ ማቴ፡3፥10
- የሚያፈራውን አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል፡- እግዚአብሔር ሕጉን ትእዛዙን የሚጠብቀውን ሰው በረድኤት ይጠብቀዋል፣ አጋንንትን ያርቅለታል፡፡
- እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተ ቅርንጫፎች ናችሁ /5/
  - ❖ ቅርንጫፍን የሚያስገኝ ግንድ ነው፡፡
  - ❖ ግንድ የቅርንጫፍ /የቅጠል ሁሉ ተሸካሚ ነው፡፡

  } በእርሱ ተደግፈን የመኖራችን
  - ❖ ግንድ ሳይኖር ቅርንጫፍ ሊኖር አይችልም፡፡ ከሱ መገኘታችን
  - ❖ ቅርንጫፍ ሁሉ ግንዱን መምሰል አለበት፡፡ የጣፋጩ ግንድ የክርስቶስ ቅርንጫፎች እኛ ክርስቶስን መምሰል አለብን፡፡
  - ❖ አንዳንድ ቅርንጫፎች በነፋስ ወይም በሌላ ኃይል ይገነጠላሉ፡፡
- ከግንዱ ጋር የሚኖር ቅርንጫፍ፡- ይለመልማል፣ ያብባል፣ ያፈራል
- ከግንዱ የተለየ ቅርንጫፍ፡- ወደ ውጭ ይጣላል፣ ይደርቃል፣ በእሳት ይቃጠላል
- ያለእኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም /5/፡- ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንም ማድረግ አይቻልም፡፡ ወይኩን ፈቃድከ የዮናስ ታሪክ- ዓሣ ለማጥመድ ዮሐ፡21፥1-14
- እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት /12/
- ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም /13/ ሕይወትን መስጠት የፍቅር ቁንጮ ነው፡፡
- ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም /15/ ምሥጢር የሚገለጠው ለወዳጅ ነውና ሰማያዊና መለኮታዊ ምሥጢር ስለተገለጠላችሁ
- ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ሾምኋችሁ /16/፡- ዞራችሁ እንድታስተምሩ፣ እንድታሳምኑ፣ እንድታጠምቁ ሥልጣን መስጠቱን

Scanned with CamScanner

- ከኀለም ስለአያደላችሁ ስለዚህ ዓለም ያጠላችኋል /19/ ዓለም የሚለው ንብረታቸው ነው ሕገወጥ ነው፣ ያላመነውን ሕገወጥ ነው። ሌባ ሌባውን ይወዳልና።
- አገልጋይ ከጌታው አይበልጥም /20/ እናንተ ከኔ አትበልጡም። እኔን እንደጠሉኝ፣ ያንተን እንዳሳደዱኝ
- ስንጠላታቸውም ምክንያት የላቸውም /22/ የአዋቂ አጥፊም ናቸውና። እራሱ ጌታ አስተምሯቸው አላመኑምና። ሉቃ፡12፥47 ለገብርኔ ዘየአምር ፈቃደ እግዚእ...
- እኔንም አባቴንም አይተውማል፣ ጠልተውማል /24/፡- እኔን ያየ አብን አይቷል። ዮሐ፡14፥9
- በከንቱ ጠሉኝ /25/፡- በከንቱ የሚጠሉኝ ከራሴ ጠንር በዙ። መዝ፡68፥4 ተገልጦለት የተናገረው
- እኔ ከአብ ዘንድ የምልከላችሁ አጽናኝ /26/ በዚህ ቦታ እግዚአብሔር ወልድ መንፈስ ቅዱስን እኔ እልከዋለሁ ይላል። በዮሐ ምዕ፡14፥15 ደግሞ አብ እንደሚልከው ይገልጻል። በባሕርይ አንድ መሆናቸውን ያመለክታል።
- ከአብ የሚወጣና የእውነት መንፈስ /26/ መንፈስ ቅዱስ የሚወጣው ከአብ ነው። ኤልቦ ዘአእመሮሙ ለሥሉስ ቅዱስ--- ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት ሃይ አበ ም፡13፥9 ገጽ 40 ምሥጢረ ሥላሴ የተገለጠ በሐዲስ ኪዳን ነውና
- 318ቱ ሊቃውንት፡- ወአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ዘሰረጸ እምአብ፡- ሃይ አበ ምዕ፡17፥11
- ሊቁ ቅዱስ ኪራሎስ፡- መንፈስ ቅዱስሃ ወጽአ እምአብ ወአኮ እምነልእ፡- ሃይ አበ ምዕ፡91፥6 ገጽ 398
    - ወይን በተተከለ በ3 ዓመት ያፈራል
    - ጌታም 3 ዓመት አስተምሮ፣ ሞቶ፣ ተሰቅሎ ምእመናን ፍሬ ክብር አግኝተዋል።
    - ወይን ባመት ባመት አንድ አንድ ቃዳ እየጨመረ ይሄዳል።
    - እሱም እየሰፋች የምትሄድ ወንጌልን ሠራሁላችሁ ሲል ነው።

Scanned with CamScanner

ምዕራፍ 16

- እንዳትሰናከሉ፡፡ ከሚያደርስባቸው መከራ ብዛት የተነሣ ከሃያማኖታቸው እንዳይናወጡ
- ከምከራባቸው ያወጣቸኋል፡፡ ዘሌ ምን በነር...ኦሪ፡9፥22፣ ዕዝ፡10፥8 በሥርዓታቸው የማያተባበረውን ከጉባኤ ይለዩት ነበር፡፡
- የሚገላችሁ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል /2/
  - ❖ ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረው እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር መስሎት ነበር፡፡ ሐዋ፡26፥9-11፣ ገላ፡1፥13፥14
  - ❖ አሕዛብም ሐዋርያትን ሲደበድቡ ፈጣሪ የሚሉት ጣዖታቸውን እንደማገልገል ይቆጥሩት ነበር፡፡
- ወደላከኝ እሄዳለሁ /5/ ወዴት ትሄዳለህ ብሎ የሚጠይቀኝ የለም /5/ ወደ ኦሳቱ በማርግበት ጊዜ ወዴት ትሄዳለህ ብሎ የሚጠይቀኝ የለም፡፡
- ይህን ስለተናገርኳችሁ ኀዘን በልባችሁ ሞልቷል /6/ አብሮ ኖሮ መለየት..
  - ❖ ሕብስት አበርክቱ፣ ከዋለበት ውሎ.... ለሚጠይቁንስ ምን እንመልስ
- እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና /7/ አገነው .ነበርና ብቸኝነት እንዳይሰማቸው አጽናኙ /ጸራትሊጦስ/ እንደሚመጣ ያበሥራቸዋል፡፡
  አጽናኝ ምዕ፡14፥15-17 ላይ መንፈስ ቅዱስን ናዛዚ ይለዋልና፡፡
- በመጣ ጊዜ ዓለምን ይወቅሳል /8/ ዓለም የተባለ ሰው ነው፡፡
  የሚወቅሰው ስለ 3 ነገር ነው፡፡
  1. ስለ ኃጢአት፡- በኔ ስለማያምኑ ነው ብሏል፡፡ በተለያዩ ተአምራት አምላክነቱን ገልጦ አስተምሮአቸው አለማመን ኃጢአት ነውና፡፡
     - ❖ የግእዝ በግእዝ መተርጉማን፡- እኔን ስቅለው በመግደላቸው የሠሩት ኃጢአት
     - ❖ መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ ለሐዋርያት በወረደ ጊዜ በሐዋርያት አድሮ እስራኤልን ግብ.ሐዋ፡2፥14-44፣ 3፥12
     - ❖ ቅዱስ ጴጥሮስ ሲሞን የሚባለውን ግብ.ሐዋ፡8፥9-24
     - ❖ ቅዱስ ጳውሎስ በርያሱስን ግብ.ሐዋ፡13፥1-12
     - ❖ ቅዱስ ጴጥሮስ ሐናንያንና ሰጲራን ግብ.ሐዋ፡5፥1-11
  2. ስለ ጽድቅ፡- ዓለም ጽድቁን ባለመቀበሉ ነው፡፡
  3. ስለ ፍርድ፡- የዚህ ዓለም ገዥ ዲያብሎስ ስለተፈረደበት ነው ብሎ ተርጉሞታል፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ መናፍስትን ማውጣት ነው፡፡ 1ኛ ቆሮ፡12፥10
- አሁን ልትሸከሙት አትችሉም /12/፡- አታስተውሉትም፣ አትረዱትም መንፈስ ቅዱስ ሳይወርድ
- የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ይመራችኋል /13/፡- ወደ ትሩፋተ ነፍስ፣ ወደ ትሩፋተ ሥጋ መርቶ ያደርሳችኋል፡፡ ትሩፋት ማለት መንፈሳዊ ሥራን አትረፍርፎ
- የእውነት መንፈስ /13/፡- ሁሉም እውነት ተብለዋል፡፡
  አብን፡- እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንክ ምዕ፡17፥3

Scanned with CamScanner

- ጥልድን፡፡ እኔ ስለ እውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ምዕ፡18፡37
  መንፈስ ቅዱስን፡- የእውነት መንፈስ ብሎ ገለጠው ምዕ፡16፡13
  አርሱ ያከብረኛል /14/፡- የግእዝ በግእዝ መተርጉማን፡- አምላክነቱን በሰው ፪ነንድ ለመግለጥና ያለኝን ጸጋ ለእናንተ በመስጠት ያከብረኛል፡፡
- ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና /14/፡- ለወልድ ያለው ሁሉ ለመንፈስ ቅዱስ አሰወው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጦታዎችን የሚሰጥ የባህርይ አምላክ መሆኑን
- ለአብ ያለው ሁሉ የኔ ነው /15/ በህልውና አንድ መሆናቸውን
- ጥቂት ጊዜ አታዩኝም፣ ደግሞ ጥቂት ጊዜ ታዩኛላችሁ /16/፡- ከተያዘበት እስከተነሣበት፣ ከተነሣበት እስከዓረገበት
- እናንተ ታለቅሳላችሁ ዓለም ግን ደስ ይለዋል /20/፡- ጌታ ሲያገ ቅዱስ ያሬድ ተኣኃዘ አርድእት ከሳውዲሆሙ እንዘይብሉ አሌ ለነ ወይለነ እስመ ሞተ እግዚእነ፣ ዓለም የተባሉ ዓለማዊ ሥራ የሚሠሩ ፈሪሳውያን፣ ሰቃልያነ እግዚእ አይሁድ
- ነገር ግን ኀዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል /20/ ጌታ ሞትን ድል አድርጎ በተነሣ ጊዜ ቅዱስ ያሬድ "ዮም ፍስሐ ኮነ በሰንበተ ክርስቲያን እስመ ተንሥአ ክርስቶስ እመ-ታ-ን"

❖ በምትወልድ ሴት መስለ፡- ሀዘኗን ሀዘናቸው፣ ደስታዋን ደስታቸው

- አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል /23/፡- በስሜ /በእኔ/ አምናችሁ መከራዬን ሁሉ እያሰባችሁ ብትለምኑ ማለት ነው፡፡
- እኔ ስለእናንተ አብን የምለምን የምላችሁ አይደለም /26/ ምዕ፡14፡15 ላይ እኔ አብን እለምናሁ ይላል፡፡
- እናንተ ትበተናላችሁ - እስከ ዕለተ አርብና ከዕለተ አርብ በኋላ
- አብ ከኔ ጋር ስለሆነ ብቻዬን አይደለሁም /32/፡- በአምላክነቱ ከአብ ጋር አንድ ስለሆነ
- በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ /33/፡- ስለሚደርስባቸው መከራ
- እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ /33/፡- የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ዓለም የተባሉት ሰይጣን፣ ኃጢአትና ሞት ናቸው፡፡ እንዲህም ማለቱ የሐዋርያትን ልቡና ለማጽናት ነው ይላል፡፡

Scanned with CamScanner

ምዕራፍ 17

- ኢየሱስ ይህን ተናግሮ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ አነሣ፡- ይህን ተናግሮ ማለት ስሉ አብ ሊነግራቸው ቆይቶ ሊጸልይ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ አንስቶ ነው። ማቴ፡14-19፣ ሚሪ፡6፥41፣ ሉቃ፡9፥16፣ ዮሐ፡11፥41 ለእኛ አብነት ለመሆን
- ማር.ዮሐ፡- ልመና የሚያስፈልገው ባለጸጋ ሲሆን በችግራችን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ ያስተምረን ዘንድ በጸሎት ምክንያት ታሰን አወጣ።
- አባት ሆይ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ ሰዓቱ ደርሷል /2/፡- ያከብርህ ዘንድ ማለት ፈጭድህ ይፈጽም ዘንድ በሚያደርገው ታምራት የአብ አምላካዊ ክብር ይገለጣልና ሰዓቱ ደርሷል ያሰ ስቅለትን ነው።
- በሥጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠኸው /2/፡- የሥጋን አምላክ መሆን
- ልጅህን አክብረው /2/፡- አምላክነቱን በታምራት ግለጸው። ከዚያ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ ሰዓቱ ደርሷል ብሎ ነበር። እዚህ ደግሞ ልጅህን አክብረው በማለት አብ የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር እንደሚገልፅ
    - ቅዱስ ቂርሎስ፡- የሥጋ ባሕርይ ከበረ ይባላል እንጂ የቃል ባሕርይ ከበረ ሊባል አይገባም። ድርሳነ ቂርሎስ ገጽ 530
- እውነተኛ አምላክ አንተ ብቻ የሆንክ /3/ ሰዎች አማልክት ብለው የሚያመልኳቸው ብዙ ናቸው። እውነተኛው ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው።
    - 1ኛ ቆሮ፡8፥56 ነገር ሁሉ በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።
- ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርኩህ /4/፡- አከበርኩህ ማለት ባስተማርኩት ትምህርት፣ በማደርገው ታምራት አምላክነትህን ገለጽኩ። አንዱ ሳንዱ ምስክር ነው። አልቦ ዘየአምሮ ለአብ... ለእግዚአብሔርስ አልቦ ዘርእዩ ግሙራ 1፥18፣ ማቴ፡11
- ዓለም ሳይፈጠር ባንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አክብረኝ /5/ የሰውነቱን ሥራ ሠርቶ ስላጨረሰ ቅድመ ዓለም የነበረ መለኮታዊ ክብሬ ይገለጥ ሲል ነው።
    - የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ በመሞቴና በመሰቀሌ አምላክነቴን እንዳይጠራጠሩ በአንተ ዘንድ ያለውን ክብሬን ግለጽ
- ከዓለም ለሰጠኸኝ ስምህን ገለጥኩላቸው /6/፡- ሐዋርያት ከዓለም መመረጣቸውን ያመለክታል። ቅድመ ዓለም ከአንተ እንደተወለድኩና ሊያውቁት የሚገባውን ሁሉ ነገርኳቸው።
- የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቼቸዋለሁ /8/ የተሰጠው ትምህርት፣ የተደረገው ታምራት የአብም የመንፈስ ቅዱስም ነው። በህልውና አይለያዩምና።

Scanned with CamScanner

- እነ ሰዳንዚህ እሰምናለሁ ስለእነሱ ከብራለሁ /10/፡- በሞቱ የሰው ልጅን ስጦከበሩ ሞቱን ክብር ይለዋል። ስለነሱ እሞታለሁ፣ ስለነሱ እሰቀላለሁ። ይትባረክ እግዚአብሔር በሰመየ ሀማማት ወልዱ።
- ከዚህ በኋላ ከዓለም አይደለሁም /11/ የሰውነት ሥራ እንደማይሠራ ሲነግራቸው ነው።
- እንደኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው /11/ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በህልውና አንድ ናቸው። ሐዋርያትም በሃይማኖት፣ በመንፈሳዊ ተግባር አንድ እንዲሆኑ
- መጽሐፉ እንዲፈጸም ከጥፋት ልጅ በቀር /12/፡- ስለይሁዳ የተነገረው ትንቢት ለምሳሌ ሽኹቴን ለላ ይውሰዳት። መዝ፡68፥25፣ 108፥8፣ ዮሐ፡1፥20። ከጥፋት ልጅ ከይሁዳ በቀር ከሐዋርያት የጠፋ የለም።
- ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው /14/፡- በዓለማዊ ሥራ ከዓለማውያን ጋር አይተባበሩም።
    - ❖ የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ከዓለም አይደሉም ማለት በጥምቀት ሁለተኛ ተወልደዋልና ከክርስቶስ ጋር ይሳመዳሉ እንዲ ከዓለማውያን ጋር አይሳመዱም።
- በእውነት ቀድሳቸው /16/፡- የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ስጣቸው እነሱን በመጥራትህ የአንተ ወገኖች አድርጋቸው።
    - ❖ ማር ዮሐንስ፡- በነሱ ላይ የምታሳድረው ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ትዳሳን አድርጓቸው
- ቃልህ እውነት ነው /16/፡- ማር ዮሐንስ፡- ያቀመሳሙርቱ የሚናገረው ሀሰት ነው ብለው እንዳይጠራጠሩ ለማድረግ ነው።
- በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለነዚህ ብቻ አለምንም /20/፡- የጌታ ጸሎት ለሐዋርያት ብቻ ሳይሆን ላመኑበትና ለወደፊትም ለሚለምበት ሁሉ ነውና ለሐዋርያትም ወደፊት ሕገበኑን በጸሎት መጠበቅ እንደሚገባቸው አብነት ለመሆን
- የሰጠኸን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ /22/ ከእመቤታችን የነሣው ሥጋ አምላክ ሆኖ ለምእመናን ክብር መስጠቱን
    - ❖ የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ክብር የሚለው ልጅነትን ነው። ስለዚህ ወልድ የአብ የባሕርይ ልጅ እንደሆነ እኛም የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ሆነናልና ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ
- ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድከኝ የሰጠኸኝ ክብሬን 24/፡- ሰው በመሆን ክቡር አምላክ መሆኑን ገለጠ።
- ዓለም አላወቀህም እኔ ግን አወኩህ /25/፡- ዓለም ያለው ሰው በተለይ አይሁድ አላመኑብህም። አንተ በእኔ እኔ በአንተ ህልው መሆንህን እኔና አንተ አንድ መሆናችንን አላመኑብህም።
- እነዚህም አንተ እንደላክኸኝ አወቅ /25/፡- ሐዋርያት ምንም እንኳ ፍጹማን የሚሆኑ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ቢሆንም እስከአሁን በታማሩትና ዛሬም በሰሙት የወልድ ንግግር የዮሴፍ ልጅ አለመሆኑን ከእግዚአብሔር የወጣ መሆኑን ተረድተዋል ማለት ነው።

Scanned with CamScanner

- ጊዜ አትክልት ወደአለበት ስፍራ /ወደ ጌቴሰማኔ/ እንደወጣ፡- ጊዜ ወደዚህ ቦታ የ መጣ ለጸሎት ነው። በጸሎት ጊዜ የጸሎተ ቦታ ሙሪያነ እንደሚገባ ለደቀመዛሙርት ለማስተማር

  ❖ ጌታ የጸለየበትን ስፍራ ማቴና ማር ጌቴሰማኔ፣ ሉቃስ ደብረዘይት ማቴ፡26፥36፣ ማር፡14፥32፣ ሉቃ፡22፥39። ዮሐንስ ብቻ የአትክልት ሥፍራ በማለት ይገልጸዋል።

- ማንን ትፈልጋላችሁ? ባላቸው ጊዜ እንዲመደቁ ማድረጉ በፈቃዱ እንጂ በእነሱ ጉልበትና ጋሻ ጦር እንደማይያዝ ለማሳወቅ
- የቂድሮስ ወንዝ፡- በኢየሩሳሌምና በደብረ ዘይት መካከል የሚገኝ ሸለቆ ነው።
- አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ስፍራውን ያውቅ ነበር /2/፡- ወጥቶም እንደልማዱ ወደ ደብረዘይት ሄደ። ደቀመዛሙርቱም ተከተሉት። ሉቃ፡22፥39 ስለዚህ ሚስጥሮችንና የሊቀ ካህናቱን ሎሌዎች አስከትሎ መጣ።
- በችቦና በፋና መጣ ማለት ሰዓቱ ምሽት ላይ ስለሆነ ጌታን ለይቶ በሚስጥር ለማሰያዝ ነው።
- ጌታ የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ መጣ /4/፡- በአይሁድ እጅ የሚያገበትን፣ መከራ የሚቀበልበትን ጊዜ ያውቃል። ስለዚህ ወደ ተክል ቦታ ሊያዙት ሲመጡ ከተክል ቦታ ወጣ፡- ስለ 3 ነገር ነው።
  1. ሳያውቅ በድንገት ያዝነው እንዳይሉ
  2. እንዳልፈራ ለማስረዳት ለጥብዓት አብነት ለመሆን
  3. ለፍቅሮ ጸላኢት፡- እሾሁ፣ እንቅፋቱ እንዳይመታቸው
- ወደ ኃላ አፈግፍገው በምድር ላይ ወደቁ /6/፡- ፍጡር ፈጣሪን መግደል ተርቶ ከፈቱ መቆም እንኪን እንደማይችል
  ❖ ሌላው ወደፊት የሚጠብቃቸውን የመከራ ጽናት ሲነግራቸው
  ❖ ሌላው፡- መውደቃቸው ከክርስቶስ መራቃቸውን ከመ/ስ መለየታቸው
  ❖ ቅዱስ ጴጥሮስ ማልኮስን ቀኝ ጆሮውን ቆረጠ /10/፡- ቀኝ የሥልጣን ምሳሌ ነው። ሥልጣነ ክህነት፣ ሥልጣነ መንግሥት ከቤተ አይሁድ እንዳለፈ /እንደተወሰደ/ ያጠይቃል።
  ❖ ሌላው ለትንቀረጽ ይእቲ ዕገሪን...
  በዘጸ፡21፥1-6፣ ዘዳ፡15፥17 እንደተጻፈው ነጻ መውጣት የማይፈልግ አገልጋይ ጆሮው እንዲቆረጥና ለዘለዓለም አገልጋይ እንዲሆን
  ❖ ሉቃስ. ምዕ፡22፥51 ላይ ጆሮውን ዳሰሰ ፈወሰው ይላል። አፍቅሮ ጽላሎትን ሊያስተምራቸው ለማዳን እንጂ ለመግደል እንዳልመጣ
- ሰይፍህን ወደሰገባው ክተተው /አስገባው /11/፡- መንፈሳዊ ተጋድሎ በትዕግሥትና በትህትና ነው እንጂ በሰይፍ ሊሆን አይገባም። ቁጣህን ወደ ትዕግሥት
- አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣምን /11/፡- በአብ ፈቃድ የሚሞት መሆኑን፡ ዮሐ፡3፥16 እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ

Scanned with CamScanner

❖ አብ ጽሞ ሰላም መሆኑ አያሳምትምና ወልድ ተቀባይ መሆኑ በሥጋ የሚመሰ

- በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀው ደቀመዝሙር /ዮሐንስ/ ለበረኛይቱ /ጲጥሮስን አስገቢኝ ያስባያትው/ ነግሮ ጴጥሮስን አስገባው /16/
- ከሰሚያሙ አንዱ ጌታችንን በጥፊ መታው /22/፡- መጻጉሰ ነው ብለው ተርጉመዋል፡ ፡
  ❖ ኤራቅሊስ፡- የሊቀ ካህናቱ አገልጋይ ፈተና በጥፊ ሲመታው ዓጥረቱ ሁሉ ከእርሱ የተነሣ ይፈሩና ይንቀጠቀጡ ነበር፡፡
  ሃያ፡አበ፡ምዕ፡48፥3 ገጽ.154
- ጌታን ከቀያፋ ወደ ገገቦ ግቢ ወሰዱት /28/፡- ሊሊት ቀያፋ ሲመረምረው አድሮ ወደ ጲላጦስ አስወስዶታል፡፡ በወቅቱ በሮም መንግሥትና ግዛት ሥር ስለነበሩ መሣፍረስ የሚገባው ጲላጦስ ነው፡፡
- የፋሲካን በግ ይበሉ ዘንድ እንጂ እንዳይረክሱ ወደ ገገቦ ግቢ አልገቡም /28/፡- ፍዓሉ ሲቀርብ ራሳቸውን ያነጻሉ፡፡ የፋሲካን በዓል የሚያከብሩት በግ አርደው እየበሉ ነው፡፡ ስለዚህ በጉን ሳይበሉ እንዳይረክሱ የአሕዛብ ወገን ወደሆነው ወደ ጲላጦስ ግቢ መግባት አልፈለጉም፡፡ ጌታን ሊገሉ እየፈለጉ እንዳንረክስ ማለታቸው ይገርማል ብሏል፡፡ ማር ዮሐንስ
- የጌታ በስቅላት መሞት /32/1- በሮማውያን ሥርዓት በመስቀል አምሳል የፈጠሮውን ሰው በመስቀል ተሰቅሎ ሞቶ ለማዳን ወእትቢገውከ በመስቀልየ ያለው በዮሐ፡12፥32 ላይ በመስቀል ተሰቅሎ እንደሚሞት ተናግሯል፡፡
  የግእዝ በግእዝ ጌታ በመሰቀል ተሰቅሎ መሞቱን ሲገልጹ
  1. በመስቀሉ፡- የሰው ልጆች ከምድር ወደ ሰማይ ይወጡ ዘንድ
  2. ለጣያት በሚሰዋው መሥዋዕት ጠቢ የረከሰውን አየር በመስቀሉ ለመቀደስ
  3. በአየር የሚኖሩ አጋንንትን ድል ለመንሣት
  4. በገነት መካከል ባለው እንጨት /በለስ/ ኃጢአት ገብቶ ነበርና በእንጨት ላይ በመስቀል ሞትን ለማራቅና ሕይወትን ለማደስ
- መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችምና /36/ ጲላጦስን የሚያስጨንቀው የዚህ ዓለም መንግሥት ስለሆነ የአይሁድ ንጉሥ ነው ስላሉህ አትጨነቅ ሲለው ነው፡፡
  ❖ ሌላው ሰማያዊ አምላክ፣ ሰማያዊ ንጉሥ መሆኑን
- እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ /37/ ዮሐ፡1፥17 ላይ ጸጋሰ ወጽድቅ... ብሎ እንደተናገረ እውነት እላችኋለሁ እያለ ስለ እውነት ከ450 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፡፡
  ❖ ሌላው፡- የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎ ያስተማረውም በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ነው፡፡
- ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምጼን ይሰማል /37/ ጲላጦስ በሐሰት እንዳይፈርድ እያስጠነቀቀው ነው፡፡
- እውነት ምንድነው? /38/ ሌሎች የአይሁድ ንጉሥ ይሉሀል አንተ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም ትላለህ እውነቱ የትኛው ነው?
  ❖ የጌታን ድምፅ ለመስማት የእውነትን ምንነት ማረጋገጥ ፈልጓል፡፡
- የአይሁድን ንጉሥ ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ? በርባንን እያሉ ጮሁ /39፥40/

Scanned with CamScanner

በርካታ ሺን ወንበሯ ነበር /40/። አያሁድ የአድልዎ ፍርዳቸውን በአደባባይ ገለጸ።
የሰላም አለቃ ታስሮ የወንበሯ አለቃ እንዲፈታ ጠየቁ።

Scanned with CamScanner

ምዕራፍ 19

"ጽናባችሁን ስገራፈምት፣ ጉንጨንም ለጽፋት ሰጠሁ"

- ጲላጦስ ጌታን ይዞ እንደገረፈው፡- እንደሚገረፍ፡ ኢሳ፡50፥6
  - ❖ ጌታም አይሁድ አሳልፈው ለአሕዛብ እንደሚሰጡትና እንደሚገረፍ፡ ሉቃ፡18፥31
  - ❖ ምሳ፡20፥30 እንደተጻፈ ግርፋትም ወደ ሆድ ገብቶ ያቆስላል።
  - ❖ አይሁድ ወንጀለኛ ሲገርፉ ከ40 በላይ አይገርፉም ነበር። ዘዳ፡25፥1-3 ጌታን ግን ብዙ ጊዜ ገርፈውታል።
  - ❖ ድርሳነ ማህየዊ፡- አጥንቱ እስኪታይ ድረስ ገርፈውታል ይላል በጥቂር ሲያስቀምጥ 5 እልፍ ጊዜ ገርፈውታል። ይህ ማለት 50 ሺህ ማለት ነው።
  - ❖ የእሾህ አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ አኖሩ /2/ ማቴ፡27፥29፣ ማር፡15፥17 ለፍና ተሳልቆ
  - ❖ ኢሳ፡59፥17 ላይ በራሱም ላይ የማዳን ቁር አደረገ ብሎ የተናገረው ትንቢት እንዲፈጸም
  - ❖ የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ፡- አክሊለ ሦክ በራሱ ላይ ማኖራቸው የዓለምን ኃጢአት መሸከሙን፣ ሕገ አራትን በሕገ ወንጌል መፈጸሙን ያመለክታል። ለላው አክሊለ ሦክ የመርገሙን መሻር ያመለክታል። ምክንያቱም አዳም እሾህ ታብቅልብህ ተብሎ ተረግሞ ነበርና ይላል።
- በተኛ እጁ ዘንግ አስያዙት፡- ማቴ፡27፥29፡- በትር እባብ ይገደልበታል። ጌታም የቀደመውን እባብ ዲያብሎስን ድል አድርጓል።
- ቀይ ልብስ አለበሱት /2/ ማቴ፡27፥28 ልብሱን ገፈው ቀይ ልብስ ማልበሳቸው የአዳምና የሔዋን ልጅነት ተወስዶ ነበርና። ቀዩ ደምህን እናፈ፣ ደማቸውን እንደሚያፈሰው መልሰው የመጀመሪያውን ማልበሳቸው ልጅነቱ እንደተመለሰለት ያሳያል።
- በጥፊም ይመቱት ነበር /3/ ትንቢቱ ሊፈጸም መዝ፡131፥4 ለጉንጮችህም እረፍትን አልሰጥም ተብሎ
- ሌላው ቀኝ ጉንጭህን ቢመታህ ሁለተኛውን ደግሞ ስጥ ማቴ፡5፥39 ብሎ ያስተማረውን በተግባር ለመፈጸም
- ልሰቅልህ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? /10/ ምላሽ ስላልሰጠው ተናዶ ነገር ግን ምንም ኃጢአት እንዳልሠራ እራሱ መስክሮ ሊያድነው አልቻለም።
- ከላይ ካተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን የለህም /11/፡- ከእግዚአብሔር ካልተፈቀደልህ፣ እኔ ካልፈቀድኩልህ ልትገለኝ አትችልም።
  - ❖ ማር.ዮሐንስ፡- ጌታ ይህን የተናገረው የጲላጦስ ትዕቢት ይሰበር ዘንድ ነው።
- ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ የባሰ ነው /11/፡- በሐሰት የከሰሱኝ የሊቀ ካህናቱ፣ የፈሪሳውያኑ የነይሁዳ ኃጢአት ታላቅ ነው።
  - ❖ ማር.ዮሐንስ፡- በዚህ አነጋገሩ ጲላጦስም የኃጢአት ተሳታፊ መሆኑን
- ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሳር ተቃዋሚ ነው /12/፡- አይሁድ ለቄሳር መንግሥት የቆሙ መስለው ጌታን ከጲላጦስ ጋር ለማጣላት ሞከሩ እንጂ እንኳን

Scanned with CamScanner

ንጉሥ ነኝ ሊል ሕገዘቡ ሊያነግሱት በወሃዱ ጊዜ ወደ ተራራ ሸሸ፡፡ ለጲላጦስም መንግሥቱ ከዚህ ዓለም አይደለችም ብሎ እትፊጹን ነግሮታል፡፡

ጊ፣ ሲሰቀል 6 ሰዓት ያህል ነበር /14/ ማርቆስ 15፡25፡ በ3 ሰዓት ሰቀሉት ያላላል፡ ፣ ጲላጦስ ስቀሉት ብሎ የሰጣቸው በ3 ሰዓት

- ሊላው፡- መስቀሉ የተዘጋጀው በ3 ሰዓት ስለሆነ ነው እንጂ
- ጲላጦስ በነግህ ገረፈው በ3 ሰጣቸው፣ በ6 ሰቀሉት አዳም በነግህ ተፈጠረ በ3 ተኛ ሄዋንን ከጎኑ ወጣች፣ በ6 ሰዓት በደለ፡፡
  - ❖ ከገነት በወጣበት ቀን አርብ ወደ ገነት ተመለሰ፡፡
- ጊታ መስቀሉን ተሸከሙ ወደ ቀራንዮ ሄደ /17/፡- ት/ኢሳ፡9፥6 አለቅነት በጫንቃው ላይ ይሆናል እንዲል መስቀሉን በትከሻው መሸከሙ ሰይጣንን ድል የመነሳቱ ምልክት ነው፡፡
  - ❖ እሱ መስቀሉን ሊሸከም ከአዳምና ከልጅቷ ትከሻ ላይ የኃጢአት ሸክማቸውን አወረደላቸው፡፡
- ጲላጦስም የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ ብሎ ጽሮ አኖረ /19/
  - ❖ የግዕዝ በግዕዝ፡- እንዲህ ብሎ መጻፉ በአይሁድ ላይ ሊዘባበትባቸው ስለፈለገ
- በአብራይስጥና በሮማይስጥ በግሪክም ተጽፎ ነበር /21/
  - ❖ በአብራይስጥ መጻፉ፡- ለቀባህናቱ ተያፋና ለሉች አይሁድ እንዲያነቡት
  - ❖ በሮማይስጥ መጻፉ፡- ጲላጦስና ከርሱ ጋር ያሉ ለሉች ሮማውያን እንዲያነቡት
  - ❖ በግሪክ መጻፉ፡- ሄሮድስና ከርሱ ጋር ያሉ ለሉች ጽርዓውያን፣ ግሪካዉያን እንዲያነቡት
- ጭፍሮች የጌታን ልብስ ስለመካፈላቸው /23/፡- መዝ፡21፥18 ልብሶችን ለራሳቸው ተካፈሉ ተብሎ የተነገረው ት/ነቢ
  - ❖ ለ4 ተካፍለዋል፡- ወንጌል በ4ቱ መዓዘን የመነገሯ ምሳሌ ለላው 4 ሆነው ጽፈዋት አንድ ሆና የመገኘቷ ምሳሌ
- ቀሚሱን ግን ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ አንትደደው ተባለ፡፡ መዝ፡21፥18 በቀሚሲም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ ያለው
- የእናቱ እህት የቀልዮጳ ሚስት ማርያም /25/፡- እንተ ቀልዮጳ ማለት የቀልዮጳ ልጅ ማለት ነው፡፡ ቀልዮጳ የኢያቄም ወንድም ነው፡፡ ኢያቄም ሐና ከሞተች በኋላ ወንድሙ ቀልዮጳ ሲሞት ዘዳ፡25፥5 በተጻፈው መሠረት የቀልዮጳን ሚስት አግብቶ ማርያም ባውፍልያን ወልዷል፡፡
- እናቱን እነሆ ልጅሽ /24/ ይታዘዝሽ፣ ያገልግልሽ፣ ይርዳሽ

  ዮሐንስም እነኂት እናትህ አለው ትምክርህ፣ ታጽናህ፣ ታረጋጋህ ሲለው ነው፡፡
  - ❖ ልጅሽ ሲል ልጆችሽ፣ እናትህ ሲል እናታችሁ
- ጌታ ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ ተፈጸመ አለ /30/፡- መዝ፡68፥21 ለመብሌ ሐሞት ለጥማቴም ሆምጣጤ አጠጡኝ ያለው በሐሞት የተደባለቀ የወይን ጠጅ አጠጡት፡፡
- ያ ቀን የማዘጋጀት ቀን /31/ የተባለ አይሁድ በዓለ ፋሲካቸውን ለማክበር የሚዘጋጅበት ቀን ስለሆነ ነው፡፡

Scanned with CamScanner

ሥ ስንብት ጉዳት ነበርና /31/፡- ማለት ልዩ የሚሆንበት ሳይ በዓለ ፋሲካ ተጀርባ ስለሚከበር

❖ ጊዜ ንቁለቁለት ሳምንት አይሁድ በዓለ ፋሲካን የሚያከብሩበት ሳምንት ነበር፡፡ ከላይ ባነበብነው አንዱ ጎኑን በጦር ሲወጋው ደምና ውኃ ወጣ /34/፡- መጽሐፉ የምንለማመክበት፣ ደሙ የምንጠጣው

Scanned with CamScanner

ምዕራፍ 20

- ማርያም መግደላዊት ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ጌታ መቃብር እንደሄዱ
- ከሳምንቱ በመጀመሪያው በእሑድ ሰንበት /1/ እሑዱ ከ7ቱ ተኖች የመጀመሪያው ጊዜ ከተነሣበት በኋላ ሰንበት ተብሏል። እሑድን ሰንበት ያለው ዮሐንስ ብቻ
  - ማቴዎስና ሉቃስ የመጀመሪያ ቀን ማቴ፡28፥1 ሉቃ፡24፥1 ሰንበት ካለፈ በኋላ ማለት ሰንበት ያለው ቅዳሜን ነው። ማር፡16፥1
- መግደላዊት ማርያም ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች /1/
  - በመር፡16፥9 ሰባት ርኩሳን መናፍስት አድረውባት እንደነበር

1. መን/ት/እቢት 2. መን/ጽርፈት 3. መን/ትዝንጋት 4. መን/ት/ውግዘት 5.መን/ገሥፃት 6. መን/ሐሜት 7. መን/ሐሰት

  - ገና ጨለማ ሳለ መለዪያ ጨለማውን ሐያዉያን ወደ ብርሃንነት ለውጠዋላት ስለነበረ
- ድንጋዩ ከመቃብሩ ተፈንቅሎ አየች /1/፡- የድንጋዩን መፈንቀል አራቱ ሁሉ ጽፈዋል። የመቃብሩን ባዶነት የጌታን መነሣት ለሌቶች ለማስረዳት
- ኢየሱስ ይወደው ወደነበረው ወደሌላው ደቀመዝሙር /2/ የተባለ ዮሐንስ ነው። ሥዕ፡13፥23 ላይ የተብራራው
  - የግእዝ በግእዝ፡- ወዘይቤ ወነበ ካልዕኒ ረድኤ ዝኪ በእንተ ርእሱ
- ሌላው ደቀመዝሙር አስቀድሞ ከመቃብሩ ደረሰ /4/፡- አብረው ትንሣኤውን ያዩ ሙ ጴጥሮስና ዮሐንስ አብረው ቢሮጡም ቀድሞ የደረሰ ዮሐንስ ነው።
  - የግእዝ በግእዝ፡- ዮሐንስ ጴጥሮስን መትደመ ብጌታ ፍቅር ስለሚታመንለ አንድም ዮሐንስ ወጣት ስለሆነ
- በራሱ የነበረው ጨርቅ ለብቻው /7/፡- ጌታ የተከፈነበት ልብስ ከመቃብሩ ሣጢኖ ተገኝቷል።
  - የግእዝ በግእዝ፡- ልብሶቹ መገኘታቸው ጌታ አለመሠረቁን ያመለክታል። ልብሱን ትቶ መነሣቱም በትንሣኤ ዘጉባኤ ለው ሁሉ ልብስ እንደማያስፈልገውና የማያልፍ ሰማያዊ ልብስ እንደሚሰጠው ያመለክታል።
- ማርያም ግን እያለቀሰች ከመቃብሩ በስተውጭ ቆማ ነበር /11/፡- ጴጥሮስ እና ዮሐንስ የመቃብሩን ሁኔታ ተመልክተው ወደቤታቸው ሄዱ።
  - ልቧ ጌታዋን ናፍቋልና በዕለተ አርብ እስከ ቀራንዮ በዕለተ እሑድ እስከ ጎልጎታ /የመቃብር ሥፍራ/ ጌታዋን ተከተለችው።
- ሁለት መላእክት ነጭ ልብስ ለብሰው /12/፡- ለጴጥሮስ እና ለዮሐንስ ያልተገለጠ ምሥጢር ለማርያም ተገለጠ። ነጭ መልበሳቸው ቀኑ የደስታ ቀን መሆኑን ለመግለጽ ነው። ስለምን ታለቅሻለሽ ዛሬ የልቅሶ ቀን አይደለም፤ ትንሣኤውን ራሱ ጌታ አብስሯታል።
- ወደ ኋላ ዞር ስትል ጌታን ቆሞ አየችው /14/፡- ጌታ ጥላውን ሊጥልባት ዞር ብላለች።
- አንቺ ሴት ስለምን ታለቅሻለሽ? ማንንስ ትፈልጊያለሽ? /15/፡- መላእክት የተናገሩትን ጌታ ይደግምላታል፤ አታልቅሽ አላት።

Scanned with CamScanner

- የእግዚአብሔር ብዙኃኑ መስሏት ነበር /15/ መጀመሪያ የእግዚአብሔር ብዙኃኑ መሰላት በኋላ ግን ማርያም ብሎ ሥሉን በማለማት እንድታውቀው ፈቀደላት።
  - ወንጌላዊ ማርቆስ ይህንን ይህ መጀመሪያ ለማርያም እንደታየ ጽፏል። ማር፡16፡9
- ገና ወደ አባቱ አላረከውምና አትንኪኝ /17/፡- ማለት ማርያም ወደ ጌታ የቀረበች ሽቱ ልትቀባው ፈልጋ ስለነበር ሽቱ መቀባት የሚያስፈልገው የሚበላሽ ሥጋ ነው የኔ ሥጋ ግን ሕያው ነውና ሽቱ አያስፈልገውም ሊላት ነው።
  - ሌላው ገና አላመንሽኝምና አትንኪኝ በማለት ሕፀፀ ሃይማኖቷን /የሃይማኖቷን ጉድለት ነቀፈ ብለው ተርጉመዋል።
- ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ /17/፡- ልብየ የእሱ የባሕርይ አቡነመ የእኛ የጸጋ
  አምላኬ፡- የለበሰው ሥጋ ቅድመ ተዋሕዶ ፍጡር ስለሆነ ይፈጥረዋል። አምላካችሁ ማለት ይፈጥረናልና።
  - የግእዝ በግእዝ፡- ወአይቤ አቡነ ወአምላክነ፡- አባታችን፣ አምላካችን አጣለም እራሱን ከሐዋርያት ለመለየት ነው። እርሱ ከአብ ጋር በመለኮት፣ በባሕርይ አንድ ነውና።
- ከሳምንቱ ፊተኛው በመሸ ጊዜ /19/፡- አንድ ሳምንት ከእለቱድ ጀምሮ ቅዳሜ ስለሚጠናቀቅ በመሸ ጊዜ ማለት እለቱድ የትንሣኤ ዕለት ማለት ነው።
- በገዛን ቤት ጌታ መጥቶ በመካከላቸው ቆመ /19/ አይሻዳድ ደጅቹ እንደተዘጉ መግባቱ መቃብሩ በድንጋይ እንደተገጠመ መነሣቱን ሊያስረዳቸው ነው።
- ሰላም ለናንተ ይሁን አላቸው /19/፡- በገዛን ቤት ገብቶ በመካከላቸው ሲቆም በፍርሃት ላይ ፍርሃት እንዳይጨመርባቸው ሰላሜን እሰጣችኋለሁ /ዮሐ፡14፡27/ ብሏቸው ነበር።
- እጆቹንም፣ ጎኑንም አሳያቸው /20/፡- ምትሐት መስሏቸው ስለነበር
  - የግእዝ በግእዝ፡- በዚህም ትንሣኤውን አረጋገጠላቸው ብለው
- እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ /22/፡- ቅዱስ ቂርሎስ እንዲህ ማለቱ በኤዳም አፍንጫ ላይ እፍ ብሎ የሕይወት እስትንፋስ ያሳደረበት ፈጣሪ መሆኑን ለማሳወቅ ነው ብሏል። ሃይ.አበ፡ሃሥ፡73 ገጽ 272
- ዳዲሞስ የሚሉት ቶማስ የችንካሩን ምልክት በእጅቼ ካላየሁ አላምንም /25/ ማለቱ የግእዝ በግእዝ ተጠራጥሮ ነው።
  - መተርጉማንም ጥንተ ሰዱቃዊ ስለሆነ ነው ብለዋል።
- ያመንህ እንጅ ያላመንህ አትሁን /27/ ጌታ ቶማስን ባለማመኑ ገሰጸው።
- ቶማስ ጌታዬ፣ አምላኬም ብሎ መለሰለት /28/፡- የግእዝ በግእዝ ቶማስ ጌታዬ አምላኬ ማለቱ አስደናቂ የሆነ ተአምሩን ስላየ ነው።
- ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው /29/ የግእዝ በግእዝ ክርስቶስ አይተው ላመኑት ብቻ ሳይሆን ሳያዩት ለሚያምኑበትም አምላካቸው መሆኑን ያመለክታል።

Scanned with CamScanner

- በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ብዙ ምልክት /30/ በሥነንስ ብቻ ሳያሠኝ በ4ውም ያልተጻፈ የራው ልጅች አየራስ ከርስተኛ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንን እንዲያምኑ የተጻፈ ነጥቦች።

Scanned with CamScanner

ምዕራፍ 21

: በናዝሬጥያዊው ባሕር አጠገብ ሰይቀመላመራቸው እንደነገና ተግልጠላቸው እንደነገና ሦስት የትንሣኤና የዳግም ትንሣኤ ቃግልጠላቸው ስለነበር

❖ መገንዘቡ ሳልሰ እንዘ.... ሉቃ፡24፡36፣ ዮሐ፡20፡19

- ስምዖን ጴጥሮስ አሣ ሳጠምድ እሄዳለሁ
  - ❖ ከጌታ ጋር ሳሉ እያበረከቱ፣ የዳነ ሰዎች በሚያመሰኩት ገንዘብ ያን እየተመገቡ ይኖሩ ነበር። አሁን ግን ያ ሁሉ ስለሌለ አሣ ለማጥመድ
- በዚያች ሌሊት ምንም አላጠመዱም /3/፡- ያለኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም ብሎ_ቸው ነበርና ምዕ፡15፡5 ላይ ጌታ አሳ ወደ መረቡ እንዲገባ አልፈቀደም፣ በራሳቸው አሳ ለማጥመድ ስለሄዱ በራሳቸውም ማድረግ እንደማይችሉ
- ልጆች ሆይ አንዳች የሚበላ አላችሁን /5/ የሚበላ እንደሌለ እያወቀ ራሱን ሊገልጥላቸው፣ ሊመግባቸው ስለፈለገ
- መረቡን በታንኳይቱ ብስተቀኝ ጣሉት /6/ ቀኝ የመልካም ነገር ምልክት ነው። ጻድ_ሞንን በቀኙ ያቆማቸዋል።
- ወደ ምድር በወጡ ጊዜ ፍምና አሣ በላዩ ላይ ተቀምጦ እንጀራም አዩ /9/
  - ❖ ለማያውያን መላእክት ያዘጋጁት እንደሆነ 153 አሣ ተይሏል።
- ጌታም እንጀራ አንሥቶ ሰጣቸው እንዲሁም አሣውን /13/
  - ❖ አሣ ፍለጋ ሲያከሙ አድረዋል፣ እርቧቸዋልና
- ከሙታን መካከል ከተነሣ በኃላ ሲገለጥላቸው ያህ 3ኛ ጊዜ ነበር /14/
  1. የትንሣኤ
  2. የዳግም ትንሣኤ
  3. የጥብርያዶስ
- የዮና ልጅ ስምዖን ትወደኛለህን? /15/ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ ቁልፍ ይዘህ አሣ ለማጥመድ የሄድክ ስለምን ነው?
- በጎቼን አሰማራ፣ ጠብቅ፡- ለጊዜው ሐዋርያትን፣ ሰብዓ አርድእትን፣ ሰላሣ ስድስቱን ቅዱሳት አንስት ሲሾመው ፍጻሜው ምእመናንን
  - ❖ የማእገ በማእገ፡- ከወደደከኝ ለምእመናን ሕሄን ንገር፣ ትምህርቱን አስተምር፣ ልጅነትን እንዲቀበሉ አድርግ።
- አንተ ጎልማሳ ሳለህ /18/፡- በዕድሜ ሳይሆን ከአእምሮ ሕፃን ሳለህ ወገበ ልቦናህን በፍርሃት ዝናር ትታጠቃለህ።
- በሸመገልክ ጊዜ እጅህን ትዘረጋለህ /18/ በአእምሮ በሸመገልክ ጊዜ እጅህን ዘርግተህ ትሰቀላለህ።
  - ❖ ማር ዮሐንስ፡- አንተ እንደዚህ ዓለም ሰው በወጣትነት ዕርትዱ በሽምግልና እንደሚደክም አይደለም። አንተ እንደገና በስተርጅና ትጸናለህ ብሏል።
- ጌተ ሆይ ይህስ እንዴት ይሆናል? /21/፡- እኔን ተሰቅለህ መ_ት ካልከኝ ዮሐንስ እንዴት ነው የሚሞተው ማለቱ ነው።

Scanned with CamScanner

- እስከመጣላ ድረስ ያናገር ዘንድ ብዙድስ ምን አማይህ? /22/ በዓለም ሳአማኔ ተመላሽ. እስከመጣላ ድረስ በሕይወት ሥጋ እንዲኖር ብዙድ ምን አስፈሊጉተህ?

እንዲልሞት፡- 1 ማቴ፡16፥28

2. ዮሐ፡21፥22

የቅዱስ ያራድ ምስክርነት ድን፡ ገጽ 192፡

- ❖ ዮሐንስ ድንግል ዘኢጥዕመ ሞተ
- ❖ በንጽሕ ከመመላእክት ተሠርገወ ወእመሚት ከማሀሙ ሐያወ
- ❖ ንጽሐ መላእክት ለበስከ እንዘሀሉ በሥጋከ ወበእንተዝ ከመመላእክት ሐሎከ

- ጥር 4 ስንክሳር፡- እንደ ወንድሞቹ ሐዋርያት ሞትን አልተመለከም።
- ሁሉ በጸጋ ለተጸፋት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል /25/። ያመራቱ በጸጋ ፡- ሰማይና ምድር ብራና፣ አእባን መራመጫያ፣ አብሕርት ተለም፣ ዕፅዋት ብዕር፣ መላእክት /ደቂቀ አዳም/ ጸሐፍት በሆነ ጽፈው ባልፈጸሙት ነበር ብለዋል። /አንድምታው/

- ❖ ቶምፍለስ የተባለ ሊቅ፡- ሊሎች ወንጌላውያን ብዙ ተአምራት እንደተው ዮሐንስም ብዙ ተአምራትን ትጂል። ምክንያቱም ዓለም ሊሰማው አይችልምና፣ ዓለም የተባለም ሊምች ናቸው።

Scanned with CamScanner